# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

83ኛ ዓመት ቁጥር 044 ጥቅምት 14 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









## «ሀገር መገንቢያ፣ ማጽኛ እና ለልማት ማነሳሻ የሚሆን ትርክት መገንባት ያስፈልጋል»

### - ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- ሀገር መገንቢያ፣ ማጽኛ፣ ለልማት ማነሳሻና አቅመ ደካሞችን መርጃ የሚሆን ትርክት በስፋት መገንባት ያስፈልጋል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የብልጽግና ፓርቲ አመራሮች ሥልጠና ላይ «ታላቁ ትርክት» በሚል ርዕስ ሰሞኑን በሰጡት ማብራሪያ እንደገለጹት፤ ሀገር መገንቢያ፣ ማጽኛ፣ ለልማት ማነሳሻና አቅመ ደካሞችን መርጃ የሚሆን ትርክት መገንባት ያስፈልጋል።

ታላቁ ትርክት በውስጡ ብዙ ትርክቶችን ያቀፈ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ትርክቶቹ የማይጣረሱ፣ የማይገፋፉ እና ተሰብስበው የበለጸገችና የጸናች ኢትዮዮጵያን የሚፈጥሩ እንዲሁም ሁሉም ትርክት እንደጅረት ትልቁን ዓባይ የሚፈጥሩ እና ትርክቶች ተሰናስለው ታላቋን ኢትዮጵያ ለመፍጠር የማይቸገሩ ሊሆኑ ይገባል ብለዋል።

ሀገርን ወደ አንድነት እና ሁለንተናዊ እድገት ማስፈንጠር የሚችል ኃይል ከውስጡ የሚያመነጭ እና ሀገር መገንቢያ፣ ማጽኛ፣ ለልማት ማነሳሻና አቅመ ደካሞችን መርጃ የሚሆን ትርክት በስፋት መገንባት እንደሚያስፈልግ አስታውቀዋል።

«ሀገር መገንቢያ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል









## «ሠራዊቱ የሀገራችን የሉዓላዊነት የመጨረሻው ምሽግ ነው»

### - ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- መከላከያ ሠራዊቱ የሀገራችን የሉዓላዊነት የመጨረሻው ምሽግ በመሆኑ ሀገር የመጠበቅ ግዳጁን በአግባቡ ይወጣል ሲሉ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ገለጹ፡፡

ጥቅምት 15 ቀን የሚከበረውን 116ኛው የመከላከያ ሠራዊት ቀን አስመልክቶ በተዘጋጀው መርሐ-ግብር የሀገር መከላከያ ሠራዊት የሚዲያ ባለሙያዎችንና የማኅበራዊ ሚዲያ አንቂዎችን የክብር አባል አድርጓል።

በወቅቱ የተገኙት የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ፤ መከላከያ ካለ ሀገር አትፈርስም ከሌለ ደግም ትፈርሣለች። ለዚህ ነው ሕዝቡ ሠራዊቱን እንደ ዓይን ብሌኑ የሚፈልገው ብለዋል።

ሕዝባችን ልማትና ፍትሕ ያስፈልገዋል። እነዚህን ሥራዎች የሚያከናውኑት ተቋማት ቢኖሩ መልካም ነው ባይኖሩም ግን መከላከያ እስካለ ድረስ ሀገር አትፈርስም ሲሉ ተናግረዋል።

መከላከያ ሠራዊት ሕገመንግሥታዊ ነው። በኢህአዴግ ጊዜ የሚያጨቃጭቀን መከላከያ የአንድ ፓርቲ ምሽግና ፓርቲው ሲፈርስ አብሮ እንደሚፈርስ አድርጎ የማስቀመጥ ችግር ነው ያሉት ፊልድ ማርሻሉ፤ አብዮታዊ ሠራዊት የግንባታ ስትራቴጂ ታቀዶ በአዲስ መተካቱን አስታውቀዋል።

አሁን ሠራዊቱ የሁሉም ብሔርና ሕዝብ ነው። መከላከያ ማለት የሀገር ማለት ሆኗል። ይህንን ኮርቼ መናገር እችላለሁ። መከላከያ ውስጥ የየትኛውም ብሔር አባል አለ። ሁሉም የተለያዩ ቋንቋና ሃይማኖት ያላቸው የተሰባሰቡበት ተቋም ነው ሲሉ ገልጸዋል።

«ሠራዊቱ የሀገራችን ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል


ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

## በበጀት ዓመቱ 138 ሺህ ቶን ዓሣ ለማምረት ታቅዷል

### - በሩብ ዓመቱ ከ14 ሺህ ቶን በላይ ዓሣ ተመርቷል

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት 138 ሺህ ቶን ዓሣ ለማምረት መታቀዱን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ በበጀት ዓመቱ ሦስት ወራት ውስጥ ከ14 ሺህ ቶን በላይ ዓሣ መመረቱንም ገልጿል።

በግብርና ሚኒስቴር የዓሣ ሀብት ልማት ዴስክ ኃላፊ ፋሲል ዳዊት (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ የዓሣ ሀብት ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛል፡፡

እንደ ዶክተር ፋሲል ከሆነ፤ በተያዘው የ2016 በጀት ዓመት

በበጀት ዓመቱ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

## ሠራዊቱ በእሳት እየተፈተነ ራሱን የሚያበቃና ነጥሮ የሚወጣ ኃይል ነው

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- የሀገር መከላከያ ሠራዊታችን በእሳት እየተፈተነ፣ ራሱን የሚያበቃ፣ ነጥሮ የሚወጣ ኃይል ነው ሲሉ ጀኔራል ጌታቸው ጉዲና ገለጹ፡፡ 116ኛውን የሠራዊት ቀን አስመልክቶ የፓናል ውይይት ተካሂዷል፡፡

በፓናል ውይይቱ ላይ ንግግር ያደረጉት በሀገር መከላከያ ሠራዊት የመረጃ ዋና መምሪያ ኃላፊ ጀኔራል ጌታቸው ጉዲና፤ በሚከሰቱት ጥቃቅንና አነስተኛ ችግሮች ሠራዊቱ የተዳከመ የሚመስላቸው አሉ፡፡ ሆኖም መከላከያ ሠራዊታችን በእሳት እየተፈተነ፣ ራሱን የሚያበቃና ነጥሮ የሚወጣ ኃይል መሆኑንም ገልጸዋል፡፡ ሠራዊቱ በከፍተኛ ደረጃ እየተጠናከረ እየሄደ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በቁጥር፣ በጥራትና በብቃት ሰፋፊ ተጋድሎ የፈጸመ እንዳለም አመልክተው፤ የመከላከያ ሠራዊት ከለውጡ ጋር ራሱን እያደሰ ፈተናዎችን እየተጋፈጠ ውጤት እያስመዘገበ

ሠራዊቱ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል








አቶ አግደው ሞላ

# በክልሉ

## አምስት ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል የሩዝ ምርት ይጠበቃል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በመኸር ወቅት ከታረሰው 83 ሺህ 334 ሄክታር መሬት አምስት ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል የሩዝ ምርት እንደሚጠበቅ የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

በአማራ ክልል ግብርና ቢሮ የሰብል ልማትና ጥበቃ ዳይሬክተር አቶ አግደው ሞላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ክልሉ አምና ከ61 ሺህ ሄክታር መሬት ሦስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል የሩዝ ምርት ማግኘት ተችሏል።

ዘንድሮ በመኸር ወቅት 83 ሺህ 334 ሄክታር መሬት የታረሰ ሲሆን ከዚህም አምስት ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል የሩዝ ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል ያሉት አቶ አግደው፤ ዘንድሮ የታረሰው መሬት ከአለፈው የምርት ዘመን ጋር ሲነፃፀር 22 ሺህ ሄክታር መሬት ጭማሪ እንዳለው ገልጸዋል።

ጭማሪው ሩዝ የማያመርቱ አካባቢዎች በሩዝ ምርት ላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የተለያዩ ሥራዎች በመሰራታቸው ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የሚገኘው ምርት ከውጭ ሀገራት ወደ ኢትዮጵያ የሚገባውን የሩዝ ምርት መጠን ለመቀነስ የበኩሉን ሚና ይጫወታል ብለዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ ብሔራዊ የሩዝ የምርምር ተቋም በአማራ ክልል ተቋቁሟል። ክልሉ ከተቋሙ አዳዲስ የሩዝ ምርጥ ዘሮችን በመጠቀም የሩዝ ምርትና ምርታማነትን እያሳደገ ይገኛል። የክልሉ ሥነ - ምህዳር ለሩዝ ምርት ምቹ በመሆኑ በምርት ውጤታማነት ላይ ትልቅ ዕድል ፈጥሯል።

በክልሉ የሩዝ ምርትን አሁን ከሚለማው በላይ ማምረት ይቻላል ያሉት አቶ አግደው፤ የክልሉ አርሶ አደሮች በሚፈልጉት መጠን ልክ የሩዝ ዘር አለመኖሩ እና ተወዳዳሪ የሆነ የሩዝ ዝርያ ለክልሉ አርሶ አደሮች ማቅረብ አለመቻሉን እንደ ተግዳሮት አንስተዋል።

ችግሩን መፍታት ከተቻለ ከፍተኛ የሩዝ ምርት ከአማራ ክልል ማግኘት ይቻላል ሲሉም ገልጸዋል።

የማዳበሪያ እጥረት እና የክልሉ ሠላምና ጸጥታ በዘንድሮ ዓመት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች መሆናቸውንም የገለጹት አቶ አግደው፤ ክልሉ ሩዝን በስፋት ለማምረት ለአርሶ አደሩና ለአመራሩ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናና ድጋፍ ተሰጥቷል። በዚህም ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉ አሠራሮች ተግባራዊ ተደርገዋል ብለዋል።

# በኬሚካል ርጭቱ

## ከ239 ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ከግሪሳ ወፍ ማዳን ተችሏል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**



አዲስ አበባ፡- በሰብል ላይ ተከስቶ የነበረውን የግሪሳ ወፍ ለመከላከል በተካሄደው የአውሮፕላን የኬሚካል ርጭት 239 ሺህ 275 ኩንታል ምርት ማዳን መቻሉን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሚኒስቴሩ የዕፅዋት ጥበቃ መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ በላይነህ ንጉሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአማራ፣ በኦሮሚያና በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች የተከሰተውን የግሪሳ ወፍ ለመከላከል በተካሄደው የኬሚካል ርጭት 239 ሺህ 275 ኩንታል ምርት ማዳን ተችሏል።

የግሪሳ ወፍ መንጋ በአንድ ቀን ዘጠኝ ሺህ 571 ኩንታል ምርት ላይ ጉዳት የማድረስ አቅም እንዳለው አቶ በላይነህ ጠቁመው፤ የግሪሳ መንጋ በሰብል ላይ አጠቃላይ በሚቆይበት 25 ቀናት ውስጥ 239 ሺህ 275 ኩንታል ምርት ላይ ጉዳት እንደሚያደርስ አስረድተዋል።

አንድ የግሪሳ ወፍ በቀን 17 ግራም የሰብል ምርት በመመገብና በማራገፍ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል ያሉት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ መንጋው ለተከታታይ 25 ቀናት በሰብል ላይ በመቆየት ሰፊ ጉዳት እንደሚያደርስ አስገንዝበዋል።

በሦስት ክልሎች ላይ የተከሰተውን የግሪሳ ወፍ ጉዳት ለመቀነስ በ503 የግሪሳ ወፍ ማደሪያ ቦታዎች ላይ በተካሄደው የኬሚካል ርጭት ጉዳት ሊያደርስ የነበረ 56 ነጥብ ሦስት ሚሊዮን የግሪሳ ወፍ መቆጣጠር ተችሏል ብለዋል።

አቶ በላይነህ እንዳስታወቁት፤ ከ95 በመቶ በላይ የኬሚካል ርጭቱ ውጤታማ ሆኗል። ችግሩ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ አስፈላጊው የመከላከል ሥራ በመከናወኑ የተባባሰ ጉዳት ሳያስከትል ግሪሳውን መቆጣጠር ተችሏል።

የኬሚካል ርጭቱ የተካሄደው የግሪሳ ወፍ በሚሰባሰብበት የምሽትና የጠዋት ጊዜ ላይ በመሆኑ በግብርና ሥራዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳያሳድር አስፈላጊው ጥንቃቄ መደረጉን ጠቁመዋል።

ግሪሳ የደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ በወቅቱ ሰብሎችን የመሰብሰብ ሥራ በተለያዩ አካባቢዎች መከናወኑንም ገልጸዋል።

ከግሪሳ ወፍ በተጨማሪ በቀጣይ የዋግ በሽታ በሰብል ላይ እንደሚከሰት ጠቋሚ ምልክቶች መኖራቸውን ያመላከቱን አቶ በላይነህ፤ በተለይ የስንዴ ዋግ በከፍተኛ ደረጃ ሊኖር ይችላል የሚል ግምት እንዳለ አስታውቀዋል።

በኦሮሚያ፣ በአማራና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች የዋግ በሽታው እንደሚከሰት የግብርና ሳይንስ መረጃዎች ይጠቁማሉ ያሉት አቶ በላይነህ፤ የዋግ በሽታው በተለይ በክላስተር የተዘሩ አካባቢዎች ላይ ከአንዱ ወደ አንዱ ማሳ እንዳይዛመት የሁሉንም አካላት ጥረት እንደሚጠይቅ አስረድተዋል።

በሽታውን ለመከላከል በሚኒስትር መስሪያ ቤት ደረጃ የሚያስፈልገው ኬሚካል በበቂ መልኩ እንዲቀርብ ዝግጅት መደረጉንም አመላክተዋል።

የዋግ በሽታና የግሪሳ ወፍ እንዲሁም ሌሎች አውዳሚ ተባዮች በምርታማነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱበት ጊዜ በመሆኑ አርሶ አደሩ በየአካባቢው ከሚገኙ የግብርና ባለሙያዎች ጋር በመመካከር የጥንቃቄ ርምጃ ሊወስድ እንደሚገባ አሳስበዋል።

# የቴክኒክና ሙያን ሥርዓተ ትምህርት ዲጂታላይዝ ለማድረግ እየተሠራ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የቴክኒክና ሙያን ሥርዓተ ትምህርት ዲጂታላይዝ ለማድረግ የግብዓት የማሰባሰብ ሥራ እየተሠራ መሆኑን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታወቀ።

የዲጂታላይዜሽን አስተዋጽኦ ለቴክኒክና ሙያ በሚል መሪ ሃሳብ ዓለም አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ጉባኤ ትናንት ተጀምሯል።

በመድረኩ ላይ ተገኝተው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ተሻለ በሬቻ እንደገለጹት፤ የቴክኒክና ሙያን ሥርዓተ ትምህርት ዲጂታላይዝ ለማድረግ ግብዓት የማሰባሰብ ሥራ እየተሠራ ነው።

የዲጂታላይዜሽን ሥርዓት እንደ ሀገር ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት ተግባራዊ እየተደረገ ነው ያሉት ዶክተር ተሻለ፤ መድረኩ የቴክኒክና ሙያ ሥርዓተ ትምህርት፣ የመምህር ሥልጠናን ጨምሮ የመረጃ ልውውጥና፣ የአስተዳደር ግብዓት ይገኝበታል ብለዋል።

ግብዓቶችን በመጠቀም በቀጣይ የቴክኒክና ሙያን ሥርዓተ ትምህርት ዲጂታላይዝ ለማድረግ እንደሚሠራ ጠቅሰው፤ የአውሮፓና አፍሪካ ባለድርሻ አካላት የተገኙበት በመሆኑ ለዘርፉ ልምድ እንደሚወሰድበትም ገልጸዋል።

የቴክኒክና ሙያን ሥርዓት ዲጂታላይዝድ ለማድረግ ስትራቴጂ መዘጋጀቱን የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታው፤ መድረኩ ለፖሊሲ አውጪዎች የትግበራ መመሪያዎችንና ማስፈጸሚያዎችን ለማዘጋጀት የሚያግዙ ግብዓት እንደሚያስገኝ አመልክተዋል።

የቴክኒክና ሙያ የመማር ማስተማር ሂደት በዘመኑ ዲጂታል ሥርዓት መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ፤ የቴክኒክና ሙያ ሰልጣኝ ወጣቶችን ከገበያው ጋር የተሳሰሩ ለማድረግ የዲጂታላይዜሽን ሥርዓት ወሳኝ ሚና እንዳለው ተናግረዋል።

የ ጂአይዜድ (GIZ) ኢትዮጵያ ፕሮግራም ሥራ አስኪያጅ ላርስ ፊሼል በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያ መንግሥት የተጀመረውን የቴክኒክና ሙያ ዲጂታላይዜሽን ሥርዓት ዝርጋታን እንደግፋለን ብለዋል።

በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ሥርዓት ውስጥ የዲጂታላይዜሽን ሚና የጎላ ነው ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ በየትኛውም ሀገሪቱ ክፍል ላይ የሙያ ብቃት ሥልጠና ተደራሽ ለማድረግ እንደሚያስችል ገልጸዋል።

የቴክኒክና ሙያ የዲጂታል ሥርዓት ለወጣቶች ሥራ ለማፈላለግ፣ ለሀገራዊ እድገት ያለው ድርሻ ትልቅ መሆኑን ጠቅሰው፤ መድረኩ የተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ ባለድርሻ አካላት የተገኙ በመሆኑ በዘርፉ ያለው ልምድ ለመለዋወጥ የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል።

በዘርፉ ዲጂታላይዜሽንን ለማስፋፋት በርካታ ሀብት የሚጠይቅ መሆኑን አመልክተው፤ ከመንግሥት ጋር በመሆን በፋይናንስና በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚያደርጉ መሆናቸውን ጠቁመዋል።


ፎቶ፡- [illegible]
ዶክተር ተሻለ በሬቻ

# በዜጎች ላይ የሚደርሰው የሳይበር ጥቃት እየጨመረ ቢመጣም የማኅበረሰቡ ግንዛቤ ዝቅተኛ ነው

**ማህሌት ብዙነህ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በዜጎች እና በተቋማት ላይ የሚደርሰው የሳይበር ጥቃት እየጨመረ ቢመጣም ማኅበረሰቡ ለሳይበር ደህንነት ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑን የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር አስታወቀ።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና እና ባህል ግንባታ ባለሙያ አቶ ዳኛው ዋለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ የዜጎች እና የተቋማት የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት እያገደ መሄዱን ተከትሎ በዜጎች እና በተቋማት ላይ የሚደርሰው የሳይበር ጥቃት በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ይገኛል። በአንጻሩ ማኅበረሰቡ ስለ ሳይበር ደህንነት ያለው ግንዛቤ በጣም ዝቅተኛ ነው።

ለሁለት ዓመታት በተካሄደው የማኅበረሰብ የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ ጥናት የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል ያሉት አቶ ዳኛው፤ ጥናቱ ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍሎች ያካተተ እና ያማከለ ሲሆን በዚህም ዜጎችን በእውቀት፣ በአመለካከት እና በልምድ ባላቸው ግንዛቤ በመለካት የዚህም ድምር ውጤትም ከ35 በመቶ ብቻ መሆኑን ያሳየ ነው ብለዋል።

የተቋማትን እና የኅብረተሰቡን የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና በማጎልበት ያለውን ዝቅተኛ የዜጎችን የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ በትኩረት እንደሚሠራ አመልክተው፤ በዚህም ዜጎችና ተቋማት ስለሳይበር ደህንነት ተገቢው ትኩረት እንዲሰጡና ራሳቸውን




መከላከል እንዲችሉ የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል።

ሁሉንም ማህበራዊ ሚዲያ አማራጭ በመጠቀም መረጃዎችን በማሰራጨት ብሎም የግንዛቤ ማስጨበጫ እና ስልጠና ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመው፤ በተለይም የጥቃት ተጋላጭ ለሆኑ ተቋማት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሠራ አስታውቀዋል።

ሳይበር ማለት መረጃ ለማከማቸት እና ለማስተላለፍ የሚረዳ ቴክኖሎጂ ሲሆን ሰውን፣ መረጃን፣ መሠረተ ልማትን እና ቴክኖሎጂን ያስተሳሰረ ነው። የሳይበር ደህንነት የመረጃ ስርቆት፣ መጭበርበር፣ ስርጭትና መሰል ጉዳዮች ላይ ሊደርሱ የሚችሉትን የተለያዩ ጉዳቶች የመከላከል ሥራ ነው።

ማኅበረሰቡ ይህንን ከግንዛቤ በማስገባት በባለቤትነት እና በኃላፊነት እንዲሁም የተለያዩ ሥልጠናዎች ላይ በመውሰድ በእራሳቸው፣ በተቋማቸው ብሎም በሀገር ላይ ሊደርስ የሚችልን የሳይበር ጥቃት መከላከል እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የኢንፎርሜሽን ደህንነት የማረጋገጥ ሥራ ለአንድ ተቋም የሚተው ጉዳይ ባለመሆኑ ተቋማት የሳይበር ጥቃት በሚያጋጥም ወቅት ቶሎ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው ያሉት አቶ ዳኛው፤ በዚህም በቅንጅት በመሥራት ሊደርስ የሚችልን ማንኛውንም ዓይነት ጉዳት መከላከል እንደሚቻል አስታውቀዋል።

አሁን ላይ በሀገሪቱ የሳይበር ጥቃት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው ያሉት አቶ ዳኛው፤ በ2010 ዓ.ም 576 የሳይበር ጥቃት የደረሰ ሲሆን በ2015 ዓ.ም 6 ሺህ 760 የሳይበር ጥቃት ደርሷል። ይህም የሳይበር ጥቃት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንደሆነ የሚያመላክት ነው ብለዋል።

በዚያው ልክ የሀገሪቱ የመከላከል አቅም እየጨመረ መሆኑን አስታውቀው፤ በዚህም በ2015 መጨረሻ የደረሰውን የሳይበር ጥቃት ውስጥ 96 በመቶ መከላከል የተቻለ መሆኑን ተናግረዋል።

በቀጣይ መስሪያ ቤቱ የቴክኖሎጂ እና የሰው ኃይል ልማት ላይ ትኩረት እየተሠራ ነው። በዚህም ተስጥኦ ያላቸውን ዜጎች በመሳተፍ እንዲሁም ለተቋማት የክትትል እና የድጋፍ ሥራ ይሠራል። በተጨማሪም የአሠራር ሥርዓቱን በማዘመን እና ተቋማትን በማደራጀት እንደሚሠራ አቶ ዳኛው አስታውቀዋል።

# ትኩረት የሚሻው የዓይን መነጽር አጠቃቀም

**ቃልኪዳን አሳዬ**

በአንድም ሆነ በሌላ መልክ በርካቶች መነፅርን ለዕይታ ችግር ይሆን ለመዘነጥ አሊያም አደገኛ ብርሃንን ለመከላከል ይጠቀሙበታል። ታዲያ ተገልጋዮቹ የሚጠቀሙትን መነፅር በሐኪም ትዕዛዝ የሚገለገሉበት አልያም መነፅሩ የጥራት ደረጃውን በሚገባ የጠበቀ ይሆን? የሚለው ጉዳይ እምብዛም ትኩረት አይሰጠውም።

ይች ችግር ደግሞ በዓይናቸው ላይ ሊያመጣው የሚችለውን መዘዝ ሲታሰብ ጉዳዩ ትኩረት የሚሻ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። የዐይን ሕክምና ባለሙያዎች ሰዎች የዓይን መነፅር ሲጠቀሙ ባለሙያዎችን ማማከር እንደሚገባቸውና የሚጠቀሙበት መነፅር ጥራቱንና ደረጃውን የጠበቀ መሆን እንዳለበት ይመክራሉ።


በአለርት ሆስፒታል የዓይን ስፔሻሊስትና የዓይን ሕክምና ክፍል ኃላፊ ሰለሞን ቡሳ (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፤ መነፅር ሁለት ዓይነት ተግባር አለው። የመጀመሪያው የፀሐይ ብርሃንንና አቧራን ለመከላከል አገልግሎት ላይ የሚውል ነው። ሁለተኛው ተጠቃሚው ተመርምሮ በሐኪም ታዞለት የሚጠቀመውና የዕይታ መዛባትን ለማስተካከል የሚሰጥ ነው።

መነፅሮች የተለያየ የብርሃንና የጨረር መጠን ያላቸው በመሆኑ ያለ ሐኪም ትዕዛዝ መጠቀም ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል፤ መነፅሩን በማይጠቀሙበት ወቅት ዓይናቸው የፀሐይ ብርሃንን መቋቋም ስለማይችል በአግባቡ ማየት ይሳናቸዋል ይላሉ።

እንደዚሁ ጤነኛ ዓይን እያላቸው ከእነሱ የዓይን ዕይታ አቅም ጋር የማይሄድ መነፅር እየተጠቀሙ የጽሑፍ ወይም የንባብ ሥራ በሚያከናውኑበት ሰዎች የዓይናቸው ዕይታ እየደከመ እንደሚሄድ ሐኪሙ ያስረዳሉ።

መነፅር የሚደረገው በሕክምና ምርመራ እንጂ እንዲሁ ከገበያ ተገኘ ተብሎ ለጌጥም ሆነ ለሌላ አገልግሎት ማድረግ ተገቢ እንዳልሆነ ዶክተር ሰለሞን ይገልጻሉ።

የዓይን ስፔሻሊስቱ እንደሚናገሩት፤ መነፅር በየመደብሩ እንደማንኛውም ሸቀጥ በመሸጥ ላይ ይገኛል። ገዥዎች በየመደብሩ እየሄዱ አንስቶ በመለካት አማረብኝ ወይስ አላማረብኝም እያሉ ገዝተው ይጠቀሙታል። ሻጮቹም ቢሆኑ በዘርፉ ያልሰለጠኑ በመሆናቸው የፀሐይ ነው፣ የማንበቢያ ነው፣ አምሮብሃል ወዘተ.... እያሉ በዘፈቀደ መሸጣቸውን ቀጥለዋል።



መነፅሮቹ ሲታዘዙ ግን በሕክምና ምርመራ ወቅት የአንደኛው ዓይንና የሌላኛው ዓይን የዕይታ መጠን የሚለያይበት ሁኔታ ስላለ ይህንንም ታሳቢ በማድረግ ነው ይላሉ።

ወቅቱ የቴክኖሎጂ በመሆኑ ሕፃናት ሳይቀሩ በስልክ፣ በቴሌቪዥን፣ በኮምፒዩርና ሌሎች የቴክኖሎጂ ተዋጽዕኖዎች ውስጥ ሆነው ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ ያሉት ሐኪሙ፤ ከስልክም ሆነ ኮምፒዩተር የሚወጣው ጨረር ወደ ዓይን በሚገባበት ወቅት የመመልከቻ ማዕከል የሆነውን የዓይን ርግብ እክል በመፍጠር የዕይታ መጠንን ይቀንሳል ሲሉ አስረድተዋል።

በዚህም በዕድሜ ርዝመት የሚመጣው የዕይታ ማነስ አሁን ላይ ዕድሜያቸው ከ20 እስከ 30 ባሉ ወጣቶች ላይም እየተከሰተ እንደሆነ ዶክተር ሰለሞን ያብራራሉ።

ሰዎች የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በሚጠቀሙበት ወቅት ለዓይናቸው እረፍት እየሰጡ ሊሆን እንደሚገባ አሳስበዋል።

እንደ ዶክተር ሰለሞን ማብራሪያ፤ ለፀሐይ ብርሃን፣ ለአቧራና ለመዘነጥም ቢሆን መነፅር መጠቀም የሚፈልግ ሰው ባለሙያን አነጋግሮ መጠቀም አለበት።

በኢትዮጵያ በተደረገ ጥናት አንድ ነጥብ ስድስት በመቶ የሚሆኑት የዕይታ ችግር ያለባቸው ሲሆኑ፤ ሰባት ነጥብ ስምንት በመቶ ዜጎች ደግሞ አነጣጥሮ የማየት እክል አለባቸው። ከዚህ መነሻነት ተመርምሮ እራስን ማወቅና መነፅር መጠቀም ተገቢ ነው ይላሉ።

በራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታል የዓይን ሐኪም የሆኑት አቤነዘር ሀብታሙ በበኩላቸው እንደሚገልጹት፤ ደረጃውን ያልጠበቀ የዓይን መነጽርን መጠቀም እንዲሁም ያለ ሕክምና ባለሙያ ትዕዛዝ መነፅሩን መጠቀም የዓይን መንሸዋረር፣ ደብዛዛ ዕይታና ራስን የማዞር፣ ከፍተኛ የራስ ምታት ስሜት ያስከትላል።

በተጨማሪም ዓይንን ማሳከክና ማቃጠል፣ የዓይን ቆብ መዛልና በረጅም ጊዜ በዓይን ላይ የከፋ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችልም ያብራራሉ።

«በኢትዮጵያ አብዛኛው ማኅበረሰብ መነፅርን የቅንጦት አድርጎ ነው የሚያስበው፤ ነገር ግን መነፅር ከሐኪም ትእዛዝ ውጪ መነፅር ማድረግ በሕክምና ሊድን የሚችል የዓይን ህመምን ወደ ከፋ ደረጃ ሊያሸጋግር ስለሚችል ማኅበረሰቡ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት ሐኪም አቤነዘር ያሳስባሉ።

በአሁኑ ወቅት ኅብረተሰቡን በስፋት እያጠቁ ከሚገኙ የጤና ችግሮች መካከል የዓይን ሕመም አንዱ ሲሆን ሰዎች ያለባቸውን የዓይን ዕይታ ችግር ለዓይን ሕክምና ባለሙያዎች በዝርዝር ማስረዳት እንዳለባቸውና ለዕይታቸው የሚሆን መነጽር እንዲያዙላቸው ቢያደርጉ መልካም ነው ይላሉ።

ኅብረተሰቡ ዓይኑን ከአቧራ፣ ከፀሐይና መሰል ድርጊቶች ለመጠበቅ በሚል የሕክምና ባለሙያዎችን ሳያማክርና ሳይመረመር የሚያደርጋቸው መነፅሮች ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው ያመዝናል። አብዛኛው የዓይን ህመም በመታከምና በሐኪም ትእዛዝ በሚደረግ መነፅር መስተካከል እንደሚገባ ምክራቸውን ለግሰዋል።

«መነፅር መድኃኒት ነው፤ እንደማንኛውም ሸቀጥ በየቦታው መሸጥ የለበትም» ያሉት ሐኪሙ፤ የዓይን መነጽሮችን በባለሙያ ትዕዛዝ መጠቀም የዓይንን መድከም በመቀነስና ከዓይነ ስውርነት ይታደጋል፤ ኅብረተሰቡ የዓይኑን ደህንነት በየጊዜው በመከታተል ጤናውን መጠበቅ ይኖርበታል ሲሉ ይናገራሉ።

በተለይ ሞባይልና ኮምፒዩተር እንዲሁም ሌሎች ብርሃን አመንጪ መገልገያዎች ላይ ለረጅም ሰዓት ከመጠቀም መቆጠብ የዓይንን ጤንነት ለመጠበቅ መፍትሄ መሆኑን ይመክራሉ።

ለፀሐይ ብርሃንና ለአቧራ መከላከያ ሊውሉ የሚችሉ መነጽሮችንም በጤና ባለሙያ ምክርና እገዛ ብቻ መጠቀም እንደሚገባ ሐኪም አቤነዘር አስረድተዋል።

በዘርፉ ላይ እየታዩ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት መንግሥት ተጨማሪ ሙያተኞችን በማሰልጠን ወደ ገበያ ማስገባት እንዳለበትና ያለሙያቸው በየመደብሩና በየመንገዱ መነፅር የሚሸጡ ዜጎች ላይ ቁጥጥር ማድረግ እንዳለበት የዓይን ሐኪሞቹ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።



አቶ ወልደአብ ደምሴ

# በበጀት ዓመቱ ሁሉም የፌዴራል ተቋማት ወደ ኤሌክትሮኒክስ የግዢ ሥርዓት እንዲገቡ ይደረጋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> በተያዘው በጀት ዓመት መጨረሻ ሁሉም የፌዴራል ተቋማት ወደ መንግሥት የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓት እንደሚገቡ የመንግሥት ግዢና ንብረት አስተዳደር ባለሥልጣን አስታወቀ።

የመንግሥት ግዢና ንብረት ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ወልደአብ ደምሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በተያዘው በጀት ዓመት መጨረሻ ሁሉም የፌዴራል ተቋማት ወደ መንግሥት የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓት እንዲገቡ የሚደረግ ይሆናል። ይህም ከዚህ በፊት ከግዢ ጋር ይነሱ የነበሩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ይቀርፋል።

የመንግሥት ኤሌክትሮኒክስ የግዢ ሥርዓት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ሲደረግ ጠቀሜታዎች እንደሚኖሩት የጠቀሱት አቶ ወልደአብ፤ የመንግሥትን ሀብት ለታለመለት ዓላማ ማዋል፤ ጊዜና ወጪን መቆጠብ እና ወረቀት አልባ አሠራር እንዲፈጠር ማድረግ ዋና ዋና የአሠራር ሥርዓቱ ጠቀሜታዎች እንደሆኑ አስረድተዋል።

በተጨማሪም የንግዱን ማኅበረሰብ እንግልትን እንደሚቀንስ ጠቁመው፤ ሥርዓቱ ከነዳጅና ከሀብት አጠቃቀም አንፃር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይቀንሳል ብለዋል።

እንደ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ የመንግሥት ኤሌክትሮኒክስ ግዢ ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮ በመውሰድ ተግባራዊ የተደረገ ሥርዓት ነው። ኢትዮጵያ ሥርዓቱን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት መዘግየቷ በመንግሥት መልካም አስተዳደር ሂደት ውስጥ በርካታ ችግሮች አጋጥመዋል። ሥርዓቱ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ሲደረግ ደግሞ ችግሮቹ ሙሉ ለሙሉ ይቀረፋሉ።

አምና በመንግሥት ኤሌክትሮኒክስ የግዢ ሥርዓት ወደ ሦስት ሺህ 200 የሚጠጉ ጨረታዎች ተከናውነው፤ ወደ 56 ቢሊዮን የሚሆን የግዢ ሂደቶች መፈፀማቸውን ያስታወሱት አቶ ወልደአብ፤ ሂደቱ ከሌሎች ጥቅሞቹ ባሻገር ወረቀት አልባ በመሆኑ ለወረቀት ግዢ የሚሆን ገንዘብ ማዳን ተችሏል ሲሉ አብራርተዋል።

ዋና ዳይሬክተር እንዳሉት፤ እንደ ሀገር ከፌዴራል መንግሥት በጀት ከ60 እስከ 70 በመቶ የሚሆነው በጀት የሚውለው ግዢ ላይ ነው። ይህንን ገንዘብ ሙሉ ለሙሉ በመንግሥት ኤሌክትሮኒክስ የግዢ ሥርዓት እንዲፈጸም ይደረጋል። ስለዚህ ለመንግሥት ዕቃ የሚያቀርቡ ድርጅቶች የሥርዓቱን ጠቀሜታ በመገንዘብ እና በሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን ራሳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው።

በአሁኑ ጊዜ የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓት በ165 ፌዴራል ተቋማት ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ ተገልጿል። ባለፈው ዓመት 70 የመንግሥት ተቋማት በኤሌክትሮኒክስት ሥርዓት ግዢ መፈጸማቸውን ይታወቃል።

Inshuraansii Oromiyaa
ኦሮሚያ ኢንሹራንስ

# ለኦሮሚያ ኢንሹራንስ (አ.ማ.) ባለአክሲዮኖች በሙሉ

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ በአስመራጭ ኮሚቴ አማካኝነት እንዲከናወን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ መሠረት ታህሳስ 1 ቀን 2015 ዓ.ም. በተደረገው የኦሮሚያ ኢንሹራንስ (ኢ.ማ.) 13ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ መመረጡ ይታወሳል፡፡

በዚሁ መሠረት ኮሚቴው የዳይሬክተሮች ቦርድ እጩ አባላትን ጥቆማ ከሰኔ 19 ቀን 2015 ዓ.ም. እስከ መስከረም 18 ቀን 2016 ዓ.ም. ከባለአክሲዮኖች በመቀበል ባገኘው ጥቆማ መሠረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት እጩ የቦርድ አባላት በባለአክሲዮኖች የተጠቆሙ መሆኑን እያስታወቀ ህዳር 22 ቀን 2016 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ስካይላይት ሆቴል ለሚካሄደው 14ኛው የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ለምርጫ የሚቀርቡ መሆኑን ኮሚቴው ያሳውቃል፡፡

## ሀ. በሁሉም ባለአክሲዮን ከተጠቆሙት

1. አቶ አብርሀም ኤጀታ አኩላ
2. ወ/ሮ አልማዝ ሚደቅሳ ወሰቡ
3. አቶ ሠለሞን ገዳ ደበሌ
4. አቶ ጥሩነህ ሚጣፋ ጉታ
5. ወ/ሮ መሬም ጭብሳ ገመቹ
6. አቶ አስግድ ረጋሳ ወርጂ
7. አቶ ኖራ ዴሬሳ አቢሾ (በኦሮሚያ ቡና ገበሬዎች ሕብረት ሥራ ዩኒየን ኃላፊነቱ የተወሰነ የተወከሉ)
8. አቶ አራርሳ ረጋሳ ፈይሳ
9. አቶ ጌትነት ከባ ጫሊ
10. አቶ አምሳሉ ብዙነህ ብሩ
11. ሻ/ል አንጋሳ ዱጋሳ ኡልፋታ
12. አቶ መንግስቱ ረጋሳ ጅማ

## ለ. ተጽማጭነት በሌላቸው (non-influential) ባለአክሲዮኖች ብቻ የተጠቆሙ

1. አቶ ደጋ ጉርሜሳ ቶሌራ
2. ኢንጂ. ታመነ ታደሰ ኢርጌ
3. ወ/ሮ መአዛ ዮሐንስ ኢዶሳ
4. ወ/ሮ ስመኝ ኩማ ሆራ
5. አቶ መሰለ ስዩም አያኖ
6. ቀሲስ በላይ መኮንን ባለሚ

## ሐ. ተጠባባቂዎች

1. አቶ ደረጀ ደጀኔ እንግዳሸት
2. አቶ ደርቤ አስፋው ሁሪሳ
3. አቶ ቶለሳ ደሜ ጅማ

## የኦሮሚያ ኢንሹራንስ (አ.ማ.)
## የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ

# ርዕሰ አንቀፅ

## የድል ዓርማ የሆነው መከላከያ ሠራዊታችን በፈተና ውስጥ እየጸና የሚቀጥል የሀገር ዋልታ ነው!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሉአላዊነቱ ቀናኢ ነው። በየዘመናቱም ከውስጥና ከውጭ የተቃጡ ሉአላዊነትንና የግዛት አንድነትን የሚፈታተኑ ተግባራትን በጽኑ ታግሎ ሀገሪቱን ከነሙሉ ክብሯ ለአሁኑ ትውልድ አስረክቧል። የአሁኑ ትውልድም የአባቶቹን አደራ በመረከብ የሀገሪቱን ሉአላዊነትና የግዛት አንድነት በደሙና በአጥንቱ አስከብሯል፤ በማስከበርም ላይ ይገኛል።

ከጥንት እስከ ዛሬ  የቅርብ እና የሩቅ ጠላቶች  ከሀገር ውስጥ ባንዳዎች ጋር ተባብረው ኢትዮጵያን ለመበታተን መሄድ እስከሚችሉት ድረስ ተጉዘዋል። በተለይም ዘመን አመጣሾቹ የኢትዮጵያ ጠላቶች ለዘመናት አብሮ የኖረውን ሕዝብ በብሔርና በሃይማኖት በመከፋፈል እርስ በእራሱ እንዳይተማመንና በሂደትም በሚኖሩ ግጭቶች ኢትዮጵያ እየተዳከመች እንድትሄድ ያለማሰለስ በመሥራት ላይ ይገኛሉ።

የውጭና የውስጥ ጠላቶች በአንድነት በማበር ለሀገሪቱ መዳከምና በሂደትም መፈራርስ አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚሉትን ኃይል በማደራጀት፤ በማስታጠቅና በማሠልጠን ታሪካዊ ጠላትነታቸውን በገሃድ ሲያስመሰክሩ ኖረዋል።

እነዚህ የውጭና የውስጥ ጠላቶች የዚህን ኩሩ ሕዝብ የዘመናት ዕሴቶች ለመናድ ሲሯሯጡ ይታያሉ። ልዩነቶችን ጌጡ አድርጎ የኖረውን ሕዝብ እርስ በእራሱ እንዳይተማመን እና እንዲጋጭ የሚያደርጉ ትርክቶችን በመፍጠር በሀገሪቱ ሁከትና ብጥብጥ እንዲነግስ ያለመታከት በመሥራት ላይ ይገኛሉ። ብዙዎቹ ፖለቲከኞች ነን ባዮች የራሳቸው አንድም ሃሳብ ሳይዙ በተላላኪነትና በባንዳነት ጎራ ተሰልፈው አንዱን ብሔር በሌላው ላይ በማስነሳት ሀገርን ለማፍረስ  ቆርጠው ተነስተዋል።

በዚህም የዜጎችን በሠላም የመኖር መብት አደጋ ላይ የጣሉና የሀገርን ሠላምና ደህንነት የሚያውኩ ሙከራዎችም ተከስተዋል። በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በጋምቤላ፣ በቤኒሻንጉልና በደቡብ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች በነዚሁ የጥፋት ኃይሎች አማካኝነት በርካታ ዜጎች ተገድለዋል፤ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፤ ለአስከፊ ሕይወት ተጋልጠዋል።

ሆኖም ከሕዝብ አብራክ በወጣው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ተጋድሎ  የእነዚህ የጥፋት ኃይሎች ሴራ በየጊዜው በማክሸፍ ላይ ይገኛል። መከላከያ ሠራዊት በዱር በገደሉ በሚያደርገው ተጋድሎ ኢትዮጵያ ከነሙሉ ክብሯ ጸንታ ቀጥላለች።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ጀግንነት መለያው፤ ድል ማድረግ ዓርማው ነው። የኢትዮጵያ  መከላከያ ሠራዊት በተሰማራበት የግዳጅ ቀጣና  የማይደረምሰው ተራራ፤ የማይወጣው አቀበት የማያሸንፈው  ጠላት የለም። ይህን እንኳንስ ወዳጅ ጠላትም የሚመሰክረው ነው።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ከሕዝብ  አብራክ የወጣ በመሆኑ ሁልጊዜም ሕዝባዊና ሀገራዊ ተልዕኮዎችን አንግቦ ይንቀሳቀሳል። የሀገሪቱን ሉአላዊነትን ለማስከበርና የዜጎችን ሠላም ለማረጋገጥ መስዋዕትነትን ይከፍላል። በዱር በገደሉ ይዋደቃል። ደሙን ያፈሳል፤ አጥንቱን ይከሰክሳል።

የመከላከያ ሠራዊት አልፋና ኦሜጋ የሀገር ሉአላዊነትና የሕዝብ ደህንነት ናቸው። የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በጀግንነቱ ሁሉም በአንድ ድምጽ የሚስማማበት በሠላም ጊዜ የልማት አርበኛ ለድንገተኛ ክስተት የማይበገር ጀግና ሠራዊት ነው። ሠራዊቱ እንደ ተኩላ በኅብረት የሚያጠቃ እንደ አንበሳ ቦታውን የማያስደፍር ጀግና መሆኑንም ብዙዎች ይስማሙበታል። ሠራዊቱ ድል የሚፈጥር፣ ሞትን የሚያሸንፍ፣ ለድንገተኛ ክስተት የማይበገር፣ ፍላጎቱን ለዓላማው የሚያስገዛ፣ የነፃነትን ዋጋ ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ ጨለማን ማሻገር የሚችል  ልበ ሙሉ ነው።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በየጦር ውሎው በጀግንነት እየተዋጋ ለእናት ሀገሩ ተሠውቷል። ለሀገርና ለወገን ያለውን አጋርነት በንግግር ሳይሆን በተግባር አሳይቷል።

በተለይ ሠራዊታችን እንደገና ሪፎርም ከተደረገበት ካለፉት አምስት ዓመታት  ጀምሮ ሕዝባዊ ባህሪ በመላበስ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከውጭ ወራሪና ከውስጥ ባንዳዎች ሲታደግ ቆይቷል። ሠራዊታችን ደሙን አፍስሶ፤ አጥንቱን ከስክሶ በከፈለው መስዋዕትነት ሀገሪቱን ከመፈራረስ ታድጎ በብልጽግና ጎዳና እንድትጓዝም አድርጓል።

ሆኖም የውጭና የውስጥ ጠላቶች በመቀናጀት የሠራዊቱን ስም ለማጠልሸት ሲሯሯጡ  ይታያሉ። ሆኖም ከሕዝብ አብራክ የወጣውና የጀግኖች ስብስብ የሆነው የመከላከያ ሠራዊት በወሬና በአሉባልታ የሚረታና የሚናድ አይደለም።

ይልቁንም ከጊዜ ወደ ጊዜ በድል ላይ የድል አክሊል እየደረበ የሕዝብ ጥቅምንና የሀገር ሉአላዊነቱን የማስጠበቅ  ቁመና ከምንጊዜውም በላይ ጎልብቶ  ይገኛል።

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ሀገሬ፤ ስሳንቺ ካወቅነው ያሳወቅነው ብዙ ነው!

በግርማቸው ጋሻው

**የጉዞ ማስታወሻ (ክፍል ሁለት)**

ሌሊቱ ያለምንም ቅዠት ለማለፉ፤  ድህረ እንቅልፍ  ውጣ ወረድ መብዛቱ ነበር ምክንያቱ። ከልካይ የሌለው ብርሃን በመስኮት በኩል ወደ መኝታ ክፍሉ ፈንጥቋል። ለቀጣዩ ጉዞ ለመነቃቃት ሻወር ወሰድኩ፤ ቀዝቀዝ ያለው ውሃ፤ ያደረውን ድካም ጠራርጎ ወሰደው። ‘እሰይ!’ አልኩ የሚሰማኝ ያለ ሰው ይመስል። አሁን አንድ ነገር ይቀረኛል፤ ቁርስ። የተገኘውን ቀማምሼ ፤ የገበታ ለሀገር ፕሮጀክት አካል ወደሆነው የጨበራ ጩርጩራ ፓርክ ለማቅናት እየተንደረደረ ወዳለው መኪና ጥልቅ አልኩ።

ትንሽ ከማይባል ጉዞ በኋላ አንድ ስፍራ ስንደርስ ሁሉም መኪና በአንድ የመከረ ይመስል ዳር ይዞ ቆመ። የኮንታ ባህል ቡድን አባላት በባህላዊ የትንፋሽ መሳሪያዎች እየተቀባበሉ ድንቅ ዜማ ፈጠሩ። ዜማውን ተከትለው የብሔረሰቡን  ባህላዊ ልብስ የለበሱ አስር ተወዛዋዦች የተለያየ ማራኪ እንቅስቃሴ በማሳየት የሁላችንንም ቀልብ ገዝተው መያዝ ችለው ነበር። ይህ ዓይነቱ ጭፈራና ዜማ የሚቀርበው ለእንግዳ ብቻ እንደሆነ ነው የተረዳነው።

ገና ምን አይታችሁ! በሚል ይመስላል፤ በስተቀኝ በኩል ጥላማ በሆነ ስፍራ ላይ አረፍ እንድንል የዞኑ የሥራ ኃላፊዎች ጋበዙን። እንግዳ ነንና ግብዣውን ተቀብለን አረፍ አልን። እንኳን ወደ አረንጓዴ ምድር በደህና መጣችሁ። በመምጣታችሁ ደስ ብሎናል አሉ የኮንታ ዞን አስተዳዳሪ። በዚህ ሳያበቁ በዞኑ ስለሚገኙ የተፈጥሮ ሃብቶች መዘርዘር ጀመሩ። በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት እየተገነባ ስላለው የኮይሻ ፕሮጀክትና ሲጠናቀቅ  በስፍራው የሚገኘውን የተደበቀ ድንቅ የተፈጥሮ ውበት በምናብ እንድንስል አደረጉን።

እውነት ነው። ይህ የቱሪስት መዳረሻ ለምቶ ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ቱሪስቶች ሲሸጥ ዳጎስ ያለ ገቢ እንደሚያስገኝ ጥርጥር የለውም። የዞኑ አስተዳዳሪ በቃል ብዙ መናገር አልፈለጉም። ይልቁን የዞኑን ድንቅ ውበት በተግባር ገልጸው አሳዩን እንጂ። ንግግራቸውን እንዳበቁ በዞኑ የሚገኙትን የግብርና ውጤቶች ተጋበዙልን አሉ። ወለላ ማር፤ እርጎ፤ አይብ፤ ሙዝ፤ አናናስ፤ ፓፓያ፤ ማንጎ፤ ብርቱካን ወዘተ... የቀረ የግብርና ምርት የለም ማለት ይቻላል፤ ያ! ለምለም ምድር ያበቀለውን ሁሉ አቀረቡ። ማእዱ ሙሉ ነበር።

ከጥቂት እረፍት በኋላ ዋናውን የኮሮኮንች መንገድ ለቅቀን ወደ ጨበራ ጩርጩራ ፓርክ ገባን። ቀደም ሲል በዚህ  ፓርክ ውስጥ የሚገኙትን እምቅ የቱሪዝም መስቦችን የማውቃቸው ለተለያዩ ባህላዊ ዘፈኖች የቪዲዮ ክሊፕ ሆነው ነበር። በፓርኩ ውስጥ በአካል ተገኝቼ ይህን አምሳለ ገነት የሆነ ቦታ በዓይኔ በብረቱ አየሁት። ፓርኩ በ1997 ዓ.ም በኮንታና ዳውሮ ብሔረሰቦች ጥያቄና ተሳትፎ በመከለሉ ከማንኛውም ስጋት ነጻ ነው ማለት ይቻላል። ፓርኩ ለብዝሀ ሕይወትና ለዱር እንስሳት ምቹና አስተማማኝ የጥበቃ  ስፍራም እንደሆነ ይነገርለታል። በኮንታና ዳውሮዎች ለደን ያላቸው ቦታ ትልቅ ነው። አንድ ሰው አንድ ዛፍ ከመቁረጡ በፊት ሶስት ችግኖች የመትከል ግዴታ አለበት።

ወደ 1190 ካሬ ሜትር የቆዳ ስፋት መሬት የሚሸፍነው ፓርኩ፤ ከባህር ወለል በላይ በ700 እና 2800 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል። በእምቅ የተፈጥሮ ሃብቶች የተንበሸበሸው ይህ ፓርክ፤ በዓለም ዙሪያ እየተመናመነ የሚገኘው የአፍሪካ ዝሆን እንዲሁም የሌሎች ብርቅዬና ድንቅዬ  እንስሳት እና አዕዋት መገኛም ነው።

የጨበራ ጩርጩራ ፓርክ የተለያዩ የውሃ ተፋሰሶችን፤ ማለትም ወንዞች፤ ጅረቶችና ሐይቆችን የያዘ በመሆኑ ብዛት ያላቸው የዱር እንስሳት እንዲርመሰመሱበት በነጻ የፈቀደ ይመስላል። በጠዋቱ ጉብኝታችን፤ ይህንን ድንቅ ስፍራ ማየት ለሚፈልጉ ሰዎች የተገነቡና እየተገነቡ ያሉ የቱሪዝም መሠረተ ልማቶችን ተመልክተናል። መሠረተ ልማቶቹን ለማከናወን የተደረገው የቦታ መረጣና የዲዛይን ተለያይነት አስገራሚና እምቅ የተፈጥሮ ሃብቱን በጉልህ ለማሳየትም ሆነ ጊዜ ወስዶ ለመዝናናት የሚያመቹ ናቸው።

**ይ**ህ የቱሪስት መዳረሻ ለምቶ ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ቱሪስቶች ሲሸጥ ዳጎስ ያለ ገቢ እንደሚያስገኝ ጥርጥር የለውም

የፓርኩን ዙሪያ ገባ ለማየት የሚያስችለው የጥርጊያ መንገድ፤ ድልድዮች፤ የቱሪስት ማረፊያ ስፋራዎች፤ ካፌዎች፤ ሬስቶራንቶች በተመረጡ ስፍራዎች ተገንብተዋል። እየተገነቡም ነው። እነዚህ መሠረተ ልማቶች ሲጠናቀቁ የቱሪስቶችን የቆይታ ጊዜ ማራዘም ከመቻላቸውም በላይ ለአካባቢው ነዋሪዎች የሥራ እድል እንደሚፈጥሩ ሳይታለም የተፈታ ነው።

ዚጊና፤ ሾሹማና አድኮላ የሚባሉ ወንዞች በፓርኩ ውስጥ ማለፋቸው ስፍራውን  ከዓመት ዓመት ሐመልማላዊ ምድር እንዲሆን አድርጎታል። ጮፎሬ፤ ሙንአ፤ ዎንባ ፤ ካርቤላ፤ ሺቫ እና ዶኖ ሐይቆችም ውበቱን አግዝፈው የሚያወጡት የፓርኩ ሃብቶች ናቸው። ከነዚህ ሐይቆች ውስጥ በአንደኛው በየትኛውም የዓለም ክፍል የማይገኝ  “ጋራ ጨበራ” ተብሎ የሚጠራ ዓሣ ይገኛል።  ይህ ፓርክ 37 መካከለኛና ትላልቅ አጥቢ እንስሳት፤ 237 የአእዋፍ ዝርያዎች የያዘ ነው። ከተጠቀሱት የአእዋፍ ዝርያዎች

ሀገሬ፤ ስሳንቺ ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል

ፍረዱኝ


# የአርመን ህዝብ ትምህርት ቤት እና ያልተፈታው ውዝግብ

**ሙሉቀን ታደገ እና ሞገስ ተስፋ**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ስር በሚገኘው የአርመን ትምርት ቤት መዘጋት ጋር ተያይዞ መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የፍረዱኝ አምድ የምርመራ ዘገባ መሠራቱ ይታወቃል። በዘገባውም የትምህርት ቤቱ ባለቤት እኔ ነኝ የሚል አካል ማግኘት እንዳልቻልን እና ትምህርት ቤቱም ተዘግቶ ለመጠጥ ቤት አገልግሎት መዋሉን ጠቁመን ነበር።

ትምህርት ቤቱን በተመለከተ ቀደም ሲልም ሌሎች ዘገባዎች የተሰሩ ቢሆንም፤ የዚህኛው ዘገባ ለንባብ መብቃት ግን ባለቤቱ እኔ ነኝ የሚል አካል እንዲገኝ አድርጓል። ዘገባውን የተመለከቱ የትምህርት ቤቱ ባለቤቶች ነን ያሉት የማህበሩ አባላትም ትምህርት ቤቱ 'ባለቤት የለውም' መባሉ ትክክል አይደለም፤ "ባለቤቶቹ እኛ ነን" ሲሉ ወደ ዝግጅት ክፍላችን ቀርበዋል።

የትምህርት ቤቱ ባለቤቶች እኛ ነን ያሉት አካላት ትምህርት ቤቱ ለመጠጥ ቤት አገልግሎት እየዋለ ነው መባሉንም ያስተባበሉ ሲሆን፤ ሃሳባቸውን በቃል ከመግለጽም ይልቅ በጽሑፍ ማቅረብን መርጠዋል። እኛም ለዛሬው የፍረዱኝ ዓምድ እትማችን ያለፈውን ዘገባ ቀጣይ ክፍል ይዘን የቀረብን ሲሆን፤ በዚህም የትምህርት ቤቱ ባለቤቶች በጽሁፍ የሰጡትን ምላሽና ማብራሪያ፣ እንዲሁም ከሰነዶች የተገኙ መረጃዎችን በጥልቀት በመመርመር እና ከባለድርሻ አካላት የተገኙ ማስረጃዎችን ዋቢ በማድረግ እንደሚከተለው ተሰናድቷል። ምልካም ንባብ።


የኪራይ ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ ድርጅት ፡
AGENCY FOR THE ADMINISTRATION OF RENTED HOUSES
No.
አዲስ አበባ ግንቦት፡ 2 1975 ዓ.ም
Addis Ababa
P.O.B. 299
ለአርመን ኮሙኒቲ ትምህርት ቤት
አዲስ አበባ
ግልባጭ ፦
ለከተማ ልማትና ቤት ሚ/ር
ለትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
ለቀጠና አምስት ጽ/ቤት
ኪ.ቤ.አ.ድ.
አዲስ አበባ

### ከአርመን ማህበር በጽሑፍ የተሰጠ ምላሽ

ቀደም ባለው ዘገባችን ለወጣው መረጃ የአርመን ኮሚዩኒቲ ማህበር በጽሑፍ በሰጠው ምላሽ እንዳመለከተው፤ የአርመን ኮሚዩኒቲ ማህበር ትምህርት ቤት ማቲን ኬቮርኮፍ ከተባሉ አርመናዊ ከተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በ1925 ዓ.ም የህንጻ ግንባታው የተጀመረ ሲሆን፤ ግንባታው ተጠናቅቆ የመማር ማስተማር ሥራ የጀመረው በ1927 ዓ.ም ነው።

ፋሽት ጣሊያን ኢትዮጵያን ዳግም ለመውረር ጥረት ባደረገባቸው አምስት ዓመታት ወቅትም በትምህርት ቤቱ የነበሩ ተማሪዎች ሳይበተኑ የትምህርት ቤቱ ስም ቪቶሪዮ ኢማኑኤል ተብሎ ስያሜ ተሰጥቶት የትምህርት ግልጋሎት ሲሰጥ ነበር። ፋሽት ኢጣሊያን ከኢትዮጵያ በወጣ ጊዜም ይህ ትምህርት ቤት ለአርመን ኮሚዩኒቲ እንዲመለስ ተደርጓል።

በዚህ ትምህርት ቤት የአርመን ዝርያ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ከሌሎች ወንድም እና እህት ኢትዮጵያውያን ልጆች እና የልጅ ልጆች ጋር ሲማሩ ያደጉበት እና በተለይም ኢትዮጵያዊ እና አርመኖች ባህላቸውንና ቋንቋቸውን ሲወራሱበት የነበረ ተቋም ነው።

በእንደዚህ አይነት ትውልድን በመቅረጽ ለ48 ዓመታት አገልግሎት የሰጠው ትምህርት ቤት በ1975 ዓ.ም በደርግ መንግሥት ተወረሰ። በዚህም ሳቢያ ተቋሙ አሳካዋለሁ ብሎ የጀመረው ተቋማዊ ዓላማ ፈተና ገጠመው። ይህ የደርግ ርምጃ ነው እያደረ እየዋለ ታሪካዊውን ትምህርት ቤት እንዲዘጋ ያደረገው።

ትምህርት ቤቱ በባለቤትነት የተቋቋመውና ይተዳደር የነበረው በኢትዮጵያ የአርመን ማህበር ነው። አድራሻውም አርመን ቤተክርስቲያን እና በርካታ የአርመን ዜጎች የተለያዩ ግንባታዎችን እና የልማት ሥራዎችን አከናውነው ይገኙበት በነበረው /Armenian quarter/ በኋላ ላይ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 ቀበሌ 01 ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የነበረ ሲሆን፤ ትምህርት ቤቱ የተመዘገበበት የቤት ቁጥርም 726 ነው።

በኢትዮጵያ ግንባር ቀደም ከነበሩት የኮሚኒቲ ትምህርት ቤቶች መካከል አርመን ኮሚዩኒቲ ትምህርት ቤት አንዱ መሆኑን የሚገልጸው የጽሑፍ ምላሹ፤ ከ1927 ዓ.ም ጀምሮ የተደራጀ እና ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት ሲሰጥ መቆየቱን አመላክቷል። በዚህም በሀገሪቱ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ብቁ ዜጎችን በማፍራት ረገድ ግንባር ቀደም ተቋም መሆኑንና በሁሉም ኢትዮጵያውያን ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ እውቅና እንዳለው ይጠቁማል።

በደርግ ዘመነመንግሥት የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት በመ/ቁ1 /1/1/14/75፣ ግንቦት 2 ቀን 1975 ዓ.ም በተላለፈ ትዕዛዝ፤ ትምህርት ቤቱን "ለትምህርት ሚኒስቴር እንድታስረክቡ" በሚል ትምህርት ቤቱን መወረሳቸውን እና በዚህም ምክንያት የትምህርት ሥራውን ምቹ ባልሆነ የኮሚዩኒቲው ክለብ አጎራባች በሆነ ቤት ውስጥ ትምህርት እየሰጡ ለመቆየት መገደዳቸውንም ነው ጽሑፉ የሚያስረዳው።

ነገር ግን በየጊዜው የሀገሪቱ የትምህርት ጥራት እና ቁጥጥር መመሪያ እየተጠናከረ በመምጣቱ ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ጊቢ መንግሥት ለትምህርት ሥራው ያወጣውን መስፈርት ሙሉ በሙሉ ማሟላት የማይችልበት ደረጃ መድረሱን በጽሑፉ የጠቆሙት አባላቱ፤ ይሁንና ቦታው መሀል ከተማ መገኘቱና በዝቅተኛ ዋጋ አገልግሎት መስጠቱን ይፈልጉ በነበሩ ቅን ወላጆች በመታገዝ በተለያየ ጊዜ ዕውቅና ፈቃድ እድሳት እየተደረገለት መቆየቱን ያነሳሉ።

ትምህርት ቤቱ በ1925 ዓ.ም ያስገነባውን ህንጻ ከተነጠቀ በኋላ ያጋጠመውን ችግር ለመቅረፍ፣ እንዲሁም ከቁጥጥር ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የሚሰጠውን ግብረ መልስ በማገናዘብ የመዋዕለ ሕጻናትቱን ማስተማሪያ ቦታ ቀደም ብሎ የመማር ማስተማር አገልግሎት ይሰጥበት ከነበረው ጊቢው በማስወጣት የቤተ ክርስቲያኑ ንብረት በሆነ ቤት ለማዘዋወር መገደዳቸውንና የወላጅ ኮሚቴ ባሉበት 700 ሺህ ብር በላይ ወጪ በማድረግ የመዋዕለ ህፃናት ትምህርት ለመስጠት ጥረት ቢያደርጉም፣ የቁጥጥር ቢሮውን መስፈርት ማሟላት አለመቻላቸውን ጠቁመዋል።

በዚህም ሳይፈልጉ ተገደው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርት ሥልጠና እና ጥራት የሙያ ብቃት ማረጋጫ ባለሥልጣን አራዳ እና ቂርቆስ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ባስተላለፈው ውሳኔ ትምህርት ቤቱ መዘጋቱን ይገልጻሉ።

ለዚህ ሁሉ ችግር መነሻ የሆነው የደርግ መንግሥት በየትኛውም የኮሚኒቲ ትምህርት ቤቶች ላይ ያልወሰደውን ርምጃ በአርመን ትምህርት ቤት ላይ መፈጸሙ ነው ሲሉ በጽሑፍ ሃሳባቸውን የገለጹት የማህበሩ አባላት፤ ይህም ትምህርት ቤቱ ስሙን የማይመጥንና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት እንዳይችል ማድረጉን ያስረዳሉ።

ማህበሩ የተወረሰውን ህንጻ ለትምህርት ሥራ አገልግሎት አስቦ የገነባው ነበር። ህንፃው ይመለስለት ዘንድ ጥቅምት 9 ቀን 1988 ዓ.ም ለኢትዮጵያ «ፕራቬታይዘሽን ኤጀንሲ» አቤት ብሎ ነበር። ይህን አቤቱታ ተከትሎም የኢትዮጵያ «ፕራቬታይዘሽን ኤጀንሲ» ሕንጻው ከሕግ ውጭ የተወረሰ መሆኑን በማረጋገጡ ታህሳስ 12 ቀን 1992 በቁጥር 20/12/360/7524/92 በተጻፈ ደብዳቤ ሕንጻው ለአርመን ኮሚኒቲ እንዲመለስ የሚል ውሳኔ አስተላለፈ። ይሁን እንጂ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ውሳኔውን በመቃወም ለፕራቬታይዜሽን ቦርድ ባቀረበው አቤቱታ መነሻነት የትምህርት ቤቱ ሕንጻ ሳይመለስ ቀርቷል።

የደርግ መንግሥት ለ10ኛው የአብዮት በዓል ዝግጅት በግዮን ሆቴል ለማክበር በሚሰናዳበት ወቅት በሆቴሉ ቅጥር ጊቢ ውስጥ ይገኝ የነበረውን የብሄራዊ ቤተ-መንግሥት የሚባለውን ትምህርት ቤት እንዲፈርስ አደረገ። ለፈረሰው ትምህርት ቤት ተተኪ ቦታ በመስጠት የራሱን ግንባታ መገንባት ሲገባው፣ የአርመን ኮሙኒቲ ትምህርት ቤትን ህንጻ አንድ ቀን በማይሞላ የማስጠንቀቂ ደብዳቤ እንዲወረስ በማድረግ ከግዮን ሆቴል ለተነሳው ብሄራዊ ቤተ መንግሥት ትምህርት ቤት በምትክነት እንዲሰጥ ተወሰነ። በዚህም በአርመን ኮሚዩኒቲ ይማሩ የነበሩ ተማሪዎች እንዲበተኑ ተደረገ።

ይሁን እንጂ ዛሬ ላይ የቤተመንግሥት ትምህርት ቤት ተብሎ የሚጠራው ትምህርት ቤት የራሱን ህንጻ የገነባ እና ያላግባብ ከተወረሰው ትምህርት ቤታችን የለቀቀን ቢሆንም፤ አሁን ላይ ምክንያቱ በውል ባልታወቀ አግባብ የተወረሰው የትምህርት ቤት ህንጻ ለግለሰብ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። ባንጻሩም የትምህርት ጥራትና ቁጥጥር ቢሮ ትምህርት የምትሰጡበት ቦታ መስፈርቱን አያሟላም ተብሎ የኮሚዩኒቲውን ትምህርት ቤት መዘጋቱ እጅግ የሚያም ከመሆኑም ባሻገር ሀገሪቱ የተሻለ የሰው ኃይል ለማፍራት የምታደርገውን ጥረትም የሚያሰናክል ነው።

የዚህ የትምህርት ቤት ሕንጻ ቀድሞውኑ ለትምህርት አገልግሎት የተገነባ በመሆኑ ከበቂ ጊቢና ይዞታ ጋር ከ18 በላይ ክፍሎች ነበሩት። ስለሆነም አሁን ላይ ይህ ያለአግባብ የተነጠቅነው ህንጻ ቢመለስልን እና ብንሰራበት በተሻለ ጥራት እና ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት በመስጠት ያካባቢውን ወላጆች ቅሬታም መመለስ ያስችላል።

ለዚህም የተወረሰባቸውን የትምህርት ቤት ህንጻ ለማስመስ ከላይ እስከታች ለሚገኙ የተለያዩ አመራሮች በተለያዩ ጊዜያት በደብዳቤ የተጠየቀ ሲሆን፤ በቀድሞው ጊዜ ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ፣ ቀጥለውም ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንዲሁም የአዲስ ከተማ መስተዳድር ከንቲባ ለክቡር አቶ ታከለ ኡማ አቤቱታ በማቅረባቸውን ነው በጽሑፍ ምላሻቸው ያመላከቱት።

በተለይ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ ቀደም ብሎ ተወርሶ የነበረ የሁሉም አብያተ ቤተክርስቲያናት ንብረት ተመልሷል። ይሁን እንጂ የአርመን ኮሚኒቲ ንብረት የሆኑት የትምህርት ቤት፣ ቤተ-ክርስቲያን እና ባለአራት ወለል ፎቅ ሕንጻ እንዲመለስላቸው ቢጠይቁም እስካሁን መልስ አላገኙም። በተለይ የትምህርት ቤቱ ሕንጻ አለመመለስ ጥራት ያለው የትምህርት ሥራ በማቅረብ በእውቀት የታነጸ እና ክሕሎት ያለው ሀገር የሚረከብ ትውልድ የመፍጠር ዓላማቸውን እውን ለማድረግ የሚያስችላቸውን እድል ያኮላሸ ሆኗል።

ምንም እንኳን ለትምህርት ግልጋሎት የሠሩት ህንጻ ቢወረስም በእውቀት የታነጸ እና ክሕሎት ያለው ሀገር የሚረከብ ትውልድ ለመፍጠር የነበራቸው ፍላጎት ከፍተኛ በመሆኑ የመዋዕለ ህፃናቱን ክፍል ከፍተኛ ወጭ በማውጣት ግንባታ አድርገው እንደነበር ያስረዳሉ።

ነገር ግን መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም በወጣው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ እንተደዘገበው ማህበሩ የትምህርቱን መስፈርት ለማሟላት ባለመፈለጉ ትምህርት ቤቱ መዘጋቱን ያትታል ያሉት አባላቱ፤ ይህም ማህበሩ ከሠራው አድካሚ ሥራ አንጻር ዘገባው ትክክል አለመሆኑን ይናገራሉ።


በተለይ ትውልድን ገንቢ የነበረው ተቋም ወደ ትውልድ አጥፊነት (መጠጥ ቤት) እንደተቀየረ ተደርጎ የቀረበው ሪፖርት ትክክል አለመሆኑን፤ የጋዜጣውን አዘጋጆች ጭምር ቤቱን እንዲጎበኙት በማድረግ እውነታውን እንዲያውቁት ማድረጋቸውን ህዝብ ይወቅልን ሲሉ አስረድተዋል።

ህሊና ያለው ሰው እንደሚያስበው ሁሉም ልጆች በዕውቀት የበለጸጉ፤ በአካል ጥንካሬና ሥነ-ምግባር ተኮትኩተው ሊያድጉ የሚችሉት ምቹ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ፍረዱኝ

# የአርመን ህዝብ ትምህርት ቤት...






ከገጽ 6 የዞረ

የመማሪያ ከባቢ ሲኖራቸው። ለትምህርት ጥራት ምቹ ሁኔታ ሲኖር እንጂ ለወላጅ ቅርብ የሆነ ቦታ ስለሆነ ብቻ ልጆች በእውቀትና በክህሎት ተወዳዳሪ ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ አይታሰብም።

በዚህ ሁኔታ መማር ደግሞ እውቀት ሊያስገኝ አይችልም። ስለሆነም ማህበሩ ህንጻችን ያስገነባቸው የተሻለ ትምህርት ለትውልድ ለመስጠት አስቦ በመሆኑ ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ትምህርት ቤቱን ይመልስልን ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል። ትምህርት ቤቱ ከተመለሰ የተሟላ እና ደረጃውን የጠበቀ ትምህር መስጠት እንደሚችሉ አመልክተዋል።

### የአራዳና ቂርቆስ ክፍለ ከተማ የዕውቅና ፈቃድ እድሳት ጽህፈት ቤት

የአራዳና ቂርቆስ ክፍለ ከተማ የዕውቅና ፈቃድ እድሳት ጽህፈት ቤት ቡድን መሪ የሆኑት ጺዮን ጌታቸው እንደሚሉት፤ የአርመን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ጽህፈት ቤቱ ተቋሙን መምራት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ማለትም በ2012 ዓ.ም ጀምሮ የእውቅና ፈቃድ እድሳት ትምህርት ቤቱ ጥያቄ አቅርቦ በባለሙያዎች ምዘና ተደርጐለታል። ምዘና በተደረገበት ወቅት ከምድረ ጊቢው ስፋት ጀምሮ የመዘዋወሪያ ቦታና መሰል የዕድሳት ቅደመ ምልከታ ውጤት ተሰርቶለታል።

በወቅቱ ሁሉንም አሟልቶ የሚጠየቁ መስፈርቶችን አሟልቶ በመስፈርቱ መሠረት ተመዝኖ አጠቃላይ 75 እና ከዚያ በላይ ውጤት ማምጣት የነበረበት ቢሆንም፤ 58 ነጥብ ስምንት ሶስት ነው። ይህም የጊቢው አጠቃላይ ስፋት እንኳን ተይዞ መስፈርቱን አላሟላም። የቁጥጥር ባለሥልጣ መሥሪያ ቤቱ ባስቀመጠው መመሪያ መሠረት አንድ ትምህርት ቤት ማሟላት የነበረበትን መስፈርት ሳያሟላ ሲቀር ከአንድ ወር በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ምዘና ይደረግለታል።

በዚህ መሠረት የጊቢው አጠቃላይ ስፋት በድጋሚ በተለካ ጊዜ 1 ሺህ 200 ካሬ ሜትር በመሆኑ መስፈርቱን አሟልቶ ተገኝቷል። በሁለተኛው ዙር በተደረገ ምዘናም 72 ነጥብ 05 ውጤት አምጥቶ ነበር። ይህም 75 ነጥብ ማሟላት ስላልቻለ እውቅና ፈቃዱን ማደስ አልቻለም።

ስለዚህ በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሁለት ጊዜ ዕድል ተሰጥቶት ማሟላት ካልቻለ ወደ ከተማ አስተዳደሩ የትምህርት ሥልጠና፣ ጥራትና ቁጥጥር ባለሥልጣን የወደቁ ተቋማት በሚል ስም ዝርዝሩ ከውጤቱ ጋር በማድረግ ይላካል። ባለሥልጣኑም በመልካም አስተዳደር ተመልክቶ መቀጠልና አለመቀጠሉን ከህዝቡ ችግር አኳያና ነባራዊ ሁኔታ ጋር አይቶ እንዲቀጥል የሚያደርጓቸው ተቋማት አሉ። አልፎ አልፎ ያለውን ሁኔታ በማየት ከ50 በላይ ያመጡ ትምህርት ቤቶችም እንዲቀጥሉ ይደረጋል።

ምዘና ባደረገበት ወቅት የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ተከስቶ ስለነበር አርመን ትምህርት ቤት በ2013 በማስተማር ሥራው እንዲቀጥል ተደርጓል። ሆኖም ግን የትምህርት ቤቱ ባለቤቶች እንዲቀጥል ስለማይፈልጉ የሚሰጣቸውን የማስተካከያ ቼክ ሊስት ተቀብለው ከማስተካከል ይልቅ ይባስኑ እንዲቀንስ ተደረገ።

በ2014 ዓ.ም የማመልከቻ ደብዳቤ ሲያስገቡ ከበፊት የነበረውን የቦታ ስፋት አልጠቀሱም። ትምህርት ቤቱ ነባር ተቋም ሲሆን የእውቅና ፍቃድ እድሳት ሲደረግ የሚከናወነው በቼክ ሊስት ሜዳው፣ ምድረ ጊቢው እንዳለ የሚወሰድ ነው። ነገር ግን መቀጠል ስላልፈለጉ ሜዳው የከበቡ ነው የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳት ጀመሩ።

መጀመሪያውኑ መስፈርት አላሟሉም የተባሉት የከለቡ የሚሉትን ይዞታ አጠቃሎ ነው። የዕውቅና ፈቃድ እድሳት ላይ ነባር ተቋም ሲሆን የትምህርት ቤት ቼክ ሊስት ሙሉ በሙሉ ያጠቃልላል። ጥሩ አፈጻጸም ካለው ያለውን ነጥብ በመስጠት ከሌላው ደግሞ ክፍተቱን እንዲያስተካከል ዜሮ ነጥብ በማስቀመጥ የምዘና ውጤት ይሰጣል። አዲስ ተቋም ሲሆን ከጅምሩ የምድረ ጊቢ ስፋት ካላሟላ ሌሎች ቼክ ሊስቶች አይታዩም።

ለምሳሌ፣ አንድ የትምህርት ተቋም ትምህርት ቤት ለመባል እውቅና ለማግኘት አንድ ሺህ ካሬ ሜትር በላይ ቦታ ሊኖረው ይገባል። ይህን ካላሟላ እውቅና ፈቃድ አይሰጠውም። አርመን እንደ ትምህርት ቤት የምድረ ጊቢውን ስፋት 1200 ካሬ ሜትር አስመዝግቧል። ፍቃድ የተሰጠውም ከአንድ እስከ አራተኛ ክፍል ለማስተማር ስለሆነ ሲያስተምር የነበረው ከአንድ እስከ አራት ባለው ነው። ሲመዘን የነበረውም በዚህ መስፈርት ነው።

2014 ዓ.ም ቼክ ሊስት እንደገና እንዲሰራ ተደርጐ የምድረ ጊቢው ስፋት ማግኘት ከሚገባው አራት ነጥብ ማሟላት ሳይችል ቀርቶ ሁለት ነጥብ ብቻ አገኘ። ይህም የሆነው ከዚህ ወዲያ የማህበሩ ነው። ከዚህ መልስ የትምህርት ቤት የሚል ሃሳብ እያነሱ ስለመጡ ነው። ከመመገቢያ ክፍሉም ጋር ተያይዞ ሲገመገም ትምህርት ቤቱ በምዘናው ዜሮ ነጥብ ነው ያገኘው። "ይህም ተቋሙ እያሳየ ያለው እንቅስቃሴ በትምህርት ዘርፍ መቀጠል አለመፈለጉን ነው" ሲሉ ገልጸዋል።

የቀጣናው ወላጆች ትምህርት ቤቱ እንዳይዘጋ ስልሚፈልጉ ግብዓቶችን በማሟላት ድጋፍ እስከ ማድረግ ደርሰው ነበር። ይሁን እንጂ ትምህርት ቤቱ የነበረው ተነሳሽነት ዝቅተኛ ስለነበር ሊዘጋ መቻሉን ይገልጻሉ።

የባለሥልጣን ጽህፈት ቤቱ የሚያስጠብቀው የመሬት ጉዳይ ሳይሆን የትምህርት ቤት ስታንዳርድ ነው የሚሉት ኃላፊዋ፤ ተቋሙ አጠቃላይ እንቅስቃሴው በትምህር ዘርፉ መቀጠል እንደማይፈልግ በማሳየቱ ቢሮቸው ትምህርት ቤቱን በተገቢው መንገድ መዝኖ ከደረጃ በታች ሆኖ በማግኘቱ መዘጋቱን ይናገራሉ።

### መሬት ልማት አስተዳደር የይዞታ ቴክኒክ አጣሪና የካርታ ዝግጅት

ዝግጅት ክፍላችን፣ የአርመን ትምህርት ቤት ይዞታን በተመለከተ ለትምህርት ቤት ተብሎ የተሰጠን ቦታ ለሌላ ዓላማ መጠቀም የሚቻልበት አግባብ መኖርና አለመኖሩን በአራዳ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር የይዞታ ቴክኒክ አጣሪና የካርታ ዝግጅት ባለሙያ ለሆኑት አቶ አብነት አበባው ጥያቄ አቅርቧል።

አቶ አብነት፣ የባለይዞታ መብት ሲፈጠር ቤቱ በማን እንደተያዘ ለማወቅ ሲታይ የሲአይኤ መረጃ እንደሚታይ ገልጸው ፤ መብት ሲፈጠር ደግሞ የ1988 የአየር ካርታና የ1991 ዓ.ም ሲአይኤስ መረጃን መሠረት ባደረገ መልኩ መሆኑን ያስረዳሉ።

መብት ሲፈጠር የልኬት ባለሙያው መሬት ላይ ወርዶ ሲለካና ሲያጣራ ትምህርት ቤት አገልግሎት እየሰጠ መሆኑንና አለመሆኑን ለክቶ ያጣራል። ከአጣራና ካገናዘበ በኋላ የ1988 የአየር ካርታን በማየት እና መሬቱ የማን እንደሆነ ተጣርቶ በመመሪያው መሠረት መብት ይፈጠራል። በዚህ መሠረት አሁን ላይ ውዝግብ የተነሳባቸው የቤት ቁጥር 726 እና 714 የሚባሉ ቤቶች መብት የተፈጠረላቸው የጂአይኤስ እና የሲአይ ኤስ መረጃውን በመመልከት መሆኑን ያስረዳሉ። በመረጃው መሠረት አርመን ክበብ እና ትምህርት ቤት በአንድ ተቋም የሚተዳደሩ የተለያየ ይዞታዎች መሆናቸውን ይናገራሉ። የተለያዩ አገልግሎት የሚሰጡ ቦታዎች አንድ ተቋምና አንድ አካል ከሆኑ በአንድ ላይ መብት ሊፈጠርላቸው እንደሚችል ጠቁመዋል።

ለድርጅት ተብሎ ለሌላ አገልግሎት ሲጠቀም በተገኘ ባለይዞታ ላይ ምን አስገዳጅ ነገር አለ? ተብለው የተጠየቁት ባለሙያው አንድ ድርጅት ለአንድ የሆነ አገልግሎት ብሎ መሬት ከወሰደ በኋላ ለሌላ ተግባር ማዋል ቢፈልግ ሂደቱን ተከትሎ የፈለገውን የማድረግ መብት አለው። ይህ ግን የራሱ የሆነ አሠራር አለው። ይሁን እንጂ ታሪካዊ ይዘት ያላቸውን ቦታዎች ከተፈቀደላቸው አግልግሎት ውጪ ሲጠቀሙ ቢገኙ ጉዳዩን መጠየቅ ያለበት ቅርስ ጥበቃ እንጂ መሬት አስተዳደር አለመሆኑን ይናገራሉ።

### ከሰነዶች የተገኙ ማስረጃዎች

ሰነድ አንድ ፡- የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት በቁጥር መ/ቁ1/1/1/14/75 በቀን 2/9/1975 ዓ.ም ለአርመን ኮሙዩኒቲ ትምህርት ቤት የጻፈው ደብዳቤ እንደወረደ "በከፍተኛ 13 ቀበሌ 02 ውስጥ የሚገኘው የአርመን ኮሚዩኒቲ ትምህርት ቤት ለመንግሥት ሥራ ስለተፈለገ በአስቸኳይ ዛሬውኑ ከሰዓት በኋላ ትምህርት ቤቱን ለትምህርት ሚኒስቴር እንድታስረክቡ እያስታወቅሁ፤ በምትኩም ለትምህርት ቤታችሁ የሚሆን ቤት እንዲሰጣችሁ ለሚመለከተው ክፍል ትዕዛዝ የተላለፈ መሆኑን እናሳውቃለን።"

ሰነድ ሁለት ፡- የአርመን ኮሙዩኒቲ ትምህርት በቀን 3/10/2012 ዓ.ም በቁጥር AC-00032/2020 ለኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር አቤቱታ አቅርበዋል። በአቤቱታውም የአርመን ቤተክርስቲያን አገልጋዮች የተቋቋመው ባለአራት ፎቅ ቤት እና በ1975 የተወረሰው ትምህርት ቤቱ እንዲመለስላቸው ጠይቀዋል።

ሰነድ ሶስት፡- የጥራት እና ቁጥጥር ባለሥልጣን ትምህርት ቤቱን ከዘጋበት አንዱ ምክንያት በቼክ ሊስት በተቀመጠ ግምገማ ነው ። በዚህ ግምገማ ትምህርት ቤቱ እንዲዘጋ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም፤ ዋነኛ ምክንያቱ ግን ትምህርት ቤቱ ለትምህርት ያዘጋጃቸው የክፍል ስታንዳርድ መሆኑን ትምህርት ቤቱ ከተገመገመባቸው የቼክ ሊስት ሰነዶች ያሳያሉ።

### የምርመራ ቡድኑ ግኝት

ግኝት አንድ፡- ከወረዳ እና በክፍለ ከተማ ትምህርት ቢሮዎች እንዲሁም በከተማዋ የትምህርት ጥራት ቁጥጥር ባለሥጣን አዲሱ ትምህርት ቤት በ 1844 ካሬ ሜትር ጊቢ ላይ እንደሚገኝ ተደርጎ መታሰቡ ስህተት ነው። ይህ የተጠቀሰው ቦታ ለአርመን ህዝብ ማህበር ትምህርት ቤት የሚል የካርታ ስም ይሰጠው እንጂ በውስጡ ሁለት የቤት ቁጥሮችን የያዘ ነው።

በዚሁ ካርታ በቤት ቁጥር 720 የተመዘገበው የትምህርት ቤቱ ይዞታ ሲሆን በቤት ቁጥር 714 የተመዘገበው ደግሞ የአርመን ኮሙኒቲ መዝናኛ ክብብ ነው። ስለሆነም ከዚህ ቀደም ትምህርት ቤቱ ለመጠጥ ቤት መዋሉን ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰው ጥቆማ በቤት ቁጥር 714 የተመዘገበውን ቤት የአርመን ኮሙኒቲ መዝናኛ ከበብ መሆኑን ካለመረዳት የመነጨ መሆኑን ተመልክተናል።

ግኝት ሁለት፡- የምርመራ ቡድኑ የተለያዩ አካላትን ጠይቆ ባረጋገጠው የምርመራ ሥራ መሠረት 18 ክፍል ያለው እና ተወርሶ የነበረው ትምህርት ቤት አሁን ላይ ለመንግሥት የትምህርት አገልግሎት የማይሰጥ ከመሆኑም ባሻገር፤ በወር በ30 ሺ.ብር ለአንድ ድርጅት ተከራይቶ እደሚገኝ ደርሶበታል።

# ፕሮጀክቶች በጊዜ በዋጋና በጥራት እንዲጠናቀቁ የሚያስችሉ ጥናቶች ይፋ ሆኑ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በሀገሪቷ የሚሠሩ ፕሮጀክቶች በጊዜ በዋጋና በጥራት እንዲጠናቀቁ የሚያስችሉ ጥናቶች ይፋ መሆናቸውን የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

ኢንስቲትዩቱ ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚክ አሶሴሽን ጋር በመተባበር በኮንስትራክሽን ዘርፉ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችና ክፍተቶቹን ለመሙላት በማሰብ በተሠሩ ጥናቶች ዙሪያ ትናንት ውይይት አካሂዷል።

የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ኢንጅነር ታምራት ሞሉ እንዳሉት፤ በሀገሪቷ የሚሠሩ ፕሮጀክቶች በጊዜ በዋጋና በጥራት እንዲጠናቀቁ የሚያስችሉ ጥናቶች ተካሂደው ለውይይት ቀርበዋል። ይህም የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ይህንን ተግባራዊ እንዲያደርግ የተሰጠውን ኃላፊነት የመወጣት አካል ነው።

ጥናቶች በመጽሐፍ መደርደሪያ ላይ እንዲውሉ ብቻ ሳይሆን ችግር ፈቺ እንዲሆኑ ኢንስቲትዩታቸው ይሠራል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዙሪያ የሚሠሩ ጥናት እና ምርምሮች በዘርፉ ላሉ ችግሮች መውጫ መንገድ እንደሚሆኑም ነው ያመላከቱት።

ኢንጅነር ታምራት በንግግራቸው እንዳመላከቱት፤ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለበርካታ የሰው ኃይል የሥራ ዕድል የሚፈጥርና በሀገር ኢኮኖሚ ላይም አስተዋፅአዋቸው ከፍተኛ ከሆኑ ዘርፎች ውስጥ ቀዳሚ ነው። በመሆኑም ዘርፉ ባለው ድርሻ ዙሪያ የሚደረጉ ውይይቶች፣ ጥናት እና ምርምሮች ችግር ፈቺ መሆናቸውን ተናግረዋል።

በዘርፉ የሚገኙ ተዋንያን ላይ የተለያዩ ውስንነቶች እንደሚስተዋሉ ያመላከቱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ችግሮቹ በየትኞቹ ዘርፎች ላይ በስፋት እንደሚስተዋሉ የማጥራት ሥራን በመሥራት የማሟያ ከህሎት ሥልጠናዎች ስለመስጠታቸውም አንስተዋል።

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ከተመሠረተ ጀምሮ ለ22ሺህ አካላት ተግባር ተኮር ሥልጠና መስጠቱንም ኢንጅነር ታምራት ተናግረዋል።

በውይይቱ የተገኙት የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ኢንጅነር ወንድሙ ሴታ በበኩላቸው፤ የኮንስትራክሽን ዘርፉ በርካታ የሰው ኃይልን የሚሸፍን ሲሆን ዘርፉ ለኢኮኖሚ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው ብለዋል።

ዘርፉን በጥናትና ምርምር መደገፍ ለዘርፉ እድገት አስፈላጊ ስለመሆኑ የጠቀሱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ጥናቶቹ በዘርፉ በሚሠማራው የሰው ኃይልና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ባለው ድርሻ ዙሪያ የተዘጋጁ መሆናቸውንም ነው ያመላከቱት።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክ አሶሴሽን ፕሬዚዳንት ለማ ጉዲሳ (ዶ/ር) በበኩላቸው ኢንስቲትዩቱ የማኅበረሰቡን ችግር የሚያቃልሉ ጥናትና ምርምሮች ላይ ትኩረት አድርጎ እንደሚሠራ ተናግረዋል። በቀጣይም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የዚህ አካል በመሆኑ በጥናትና ምርምር እንዲደገፍ በጋራ እንሠራለን ብለዋል።



# ሠራዊቱ በእሳት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

መሆኑን አስገንዝበዋል።

ጀኔራሉ፤ ሠራዊቱ ዋጋ እየከፈለ ሀገሪቷን የማስቀጠል ጉዳይ ላይ ተጠምዶ ነው ያለው ብለዋል። ሆኖም የሀገር ጠንቅ የሆኑ ኃይሎች በሠራዊቱ ላይ በተለያየ መንገድ እንደሚዘምቱ፤ ስሙን በማጠልሸት የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ባልሆነ መንገድ እንደሚያደናግሩና አሉባልታዎችን በመንዛት አቅሙን ለማዳከም ጥረት እንደሚያደርጉ ገልጸዋል።

ከውስጥም ከውጭም የሚከሰቱ የጸጥታና ደኅንነት ችግሮች በመቋቋምና በመቀነስ ሀገራዊ ደኅንነትን አስተማማኝ በማድረግ ኢትዮጵያን የማስቀጠል ኃላፊነትን ይዞ እየሠራ እንዳለ ተናግረዋል። በዚህም ከፍተኛ መስዋዕት እየከፈለ እንዳለ ጠቅሰዋል። ይህ ብርታቱ መታሰብ ይኖርበታል ነው ያሉት።

ውትድርና ውስጥ ድካሙ ሰፊ ነው ያሉት ጀኔራሉ፤ ሠራዊቱ የጊዜ የአካልና የሕይወት መስዋዕትነትን እየከፈለ ሀገርን የማስቀጥል ኃላፊነቱን በአግባቡ እየተወጣ መሆኑን አስታውቀዋል። «አሁን እያጋጠሙ ያሉ ፈተናዎችንም በብቃት እየተወጣ ያለ ሠራዊት መሆኑንና ከቀጣናው አልፎ በአፍሪካ ደረጃ እንዲህ ዓይነት ሠራዊት ማግኘት ከባድ ነው» ብለዋል።

የግል ቡድናዊ አጀንዳ ይዘው ከሠራዊቱ ጋር የሚፋለሙ ቢኖሩም ሠራዊቱ መስዋዕትነት እየከፈለ ያለው ሀገርን ለማስቀጠል እንደሆነ ተናግረዋል። ኅብረተሰቡ ይህንን በሚገባ ተገንዝቦ ሠራዊቱንም መንከባከብ እንዳለበት አስገንዝበዋል። «አሁን ካለን ቀጣናዊና ሀገራዊ ሁኔታ ይህ ሠራዊት በጠንካራ መሠረት ሊቀጥል ይገባል። ይህንንም መላው ኅብረተሰብ ሠራዊቱን ማበረታታትና ማጠናከር ይኖርበታል» ሲሉ ገልጸዋል።

የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ወታደራዊ ጉዳዮች አማካሪ ሌተናል ጀኔራል አለምሸት ደግፌ በመርሐግብሩ ባደረጉት ገለጻ፣ የሠራዊት ቀን ሲከበር ለሠላም ከፍታ በመስጠት ነው ብለዋል።

ወጥቶ መግባት፣ ልማትና እድገት የሚኖረው ሠላም ሲሰፍን እንደሆነ ጠቅሰው፤ ሠራዊቱ ሀገር እንድትጸናና ሠላም እንዲሰፍን በተለያዩ ጊዜያት ክቡር ሕይወቱን እስከመስጠት ዋጋ መክፈሉን አንስተዋል።

ሌተናል ጀኔራል አለምሸት፤ ሠላም እንዲረጋገጥና ሕዝቡ በራሱ ሠላማዊ ኑሮውን እንዲመራ ሠራዊቱ ዛሬም ድረስ ተሰማርቶ እየሠራ እንዳለ በመግለጽ፣ የሕዝቡን የሠላም ፍላጎት ችግር ውስጥ የሚከቱ ጉዳዮች እንዲፈቱ በማድረግ ትልቁን ሚና እየተወጣ እንዳለ አመልክተዋል።

ቀኑ ሲከበርም ሠላምን ከፍ አድርጎ በማየት፣ ሀገርን የማጽናት ተጋድሎ የፈጸመውን ሠራዊት በማመስገን፣ ሠራዊቱ ከሕዝቡ ጋር ቃሉን በማደስ እንደሆነ ተናግረዋል።

ብርጋዴር ጀኔራል ተስፋዬ ሀብተማርያም በበኩላቸው፤ ሠራዊት የሚቆስለው፣ የሚደማውና የሚሞተው ለሕዝብ እንደሆነ ተናግረዋል። ይህንን ሠራዊት ስሙን ማጉደፍ ተገቢ እንዳልሆነም ገልጸዋል። ሀገሩን የሚወድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሠራዊቱን መደገፍ እንዳለበትም አስታውቀዋል።

116ኛው የሠራዊት ቀን «በተፈተነ ጊዜ የሚጸና የድል ሠራዊት» በሚል መሪ ቃል በተለያዩ ዝግጅቶች በተቋም ደረጃ እየተከበረ ይገኛል።

# በበጀት ዓመቱ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

138 ሺህ ቶን ዓሣ ለማምረት ታቅዶ፤ በሦስት ወራት ውስጥ 14 ነጥብ 27 ሺህ ቶን ዓሣ ማምረት ተችሏል።

ለዓሣ ሀብት ልማት መንግሥት ልዩ ትኩረት ሰጥቶት እየተሠራ ነው ያሉት ዶክተር ፋሲል፤ የዓሣ ሀብት ልማትን በሌማት ቱሩፋት መርሐግብሩ እንዲካተት ተደርጎ ክልሎች ዓሣ በስፋት እንዲያመርቱ የማድረግ፣ የማስተዋወቅ፣ የንቅናቄና ልዩልዩ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

በሀገሪቱ 200 የሚሆኑ የዓሣ ዝርያዎች ቢኖሩም ለገበያ እየቀረቡ የሚገኙት ከስድስት ዝርያ ያልበለጡ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ጥቅም ላይ የሚውሉ የዓሣ ዝርያዎችን በማሳደግ ወደ ገበያ ለማቅረብ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የልምድ ልውውጥ ሥራዎች ከሌሎች የልማት አጋሮች ጋር በቅንጅት እየተሠራ ነው ብለዋል።

በሀገሪቷ ለዓሣ እርባታ ምቹ የሆኑ ሐይቆችና ግድቦች ቢኖሩም ምርቱን በሚፈለገው ደረጃ ማሳደግ አልተቻለም ያሉት ዶክተር ፋሲል፤ የዓሣ ጫጩት፣ የዘመናዊ ማስገሪያ መሣሪያዎች እና ለእርባታ የሚሆን የዓሣ የመኖ አቅርቦት እጥረት ተግዳሮቶች መሆናቸውን አመልክተዋል።

በተጨማሪም የመበለቻ ቦታዎች እና ዘመናዊ የዓሣ ምርት ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች እጥረትም የምርት ሂደቱን ቀልጣፋ እንዳይሆን ማድረጋቸውን ተናግረዋል።





ዶክተር ፋሲል ዳዊት

ያሉትን ችግሮች በመፍታት ምርቱን በሚፈለገው ደረጃ ለማሳደግ እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸው፤ የዓሣ ጫጩት የብዜት ማዕከላትን የማቋቋምና በሥራ ላይ የሚገኙትን ባህርዳር፣ አርባምንጭ፣ ሐዋሳ፣ ዝዋይ፣ ባቱ፣ ሰበታ ብሔራዊ የዓሣ ምርምርና የዓሣ ጫጩት የብዜት ማዕከላትን የማጠናከር ሥራ እየተከናወነ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

የዓሣ ጫጩቶችን የማይጎዱና የእርባታ ሂደቱን የማያስተጓጉሉ ዘመናዊ የማስገሪያ መሣሪያዎች ወደሀገር ውስጥ እንዲገቡ አስፈላጊው እገዛ እየተደረገ ነው ያሉት ኃላፊው፤ አስጋሪዎችም በሕጋዊና በዘመናዊ መንገድ ዓሣ እንዲያጥምዱ ግንዛቤ እየተፈጠረላቸው መሆኑን አስረድተዋል።

ዓሣ እርባታ ሰፊ ገቢ ማመንጨት የሚያስችል ዘርፍ እንደሆነ የገለጹት ዶክተር ፋሲል፤ ሀገሪቱ በቂ የሆነ የውሃ መጠንና ተስማሚ የአየር ንብረት ያላት በመሆኑ ባለሀብቶች ወደዘርፉ በመግባት የዓሣ ምርትና ምርታማነትን በሚፈለገው ደረጃ ማሳደግ እንደሚገባ አስገዝበዋል።

የዓሣ ጫጩት አቅርቦትን በዓይነትና ጥራት በማሳደግ፣ የብዜት ማዕከላትን ማስፋፋትና ለማኅበረሰቡ ዘመናዊ የዓሣ አመራረትን በተመለከተ ግንዛቤ መፍጠር የትኩረት አቅጣጫዎች መሆናቸውን አመልክተዋል።

# «ሀገር መገንቢያ፣...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አሰባሳቢ ትርክትን ቢፈጥር የምንጠቀመው እራሳችን እና ልጆቻችን ናቸው። በመሆኑም ታላቋን ትርክት ለፖለቲካ ፍጆታ ሳይሆን ሰብሰብ ብለን እንደሀገር ለመቆም፣ ለመጽናት፣ ለመሻገር እና ለመበልጸግ ልንጠቀምበት ይገባል ብለዋል።

በታላቋ ትርክት ሃሳብ የማንሰላሰል ሂደት ውስጥ የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጠው የበለጸገች፣ ሠላማዊና ወንድማማቾች በአንድ ላይ መኖር የሚችሉባት ሀገር መፍጠር የሚለው ሃሳብ ሊሆን እንደሚገባ ገልጸዋል።

ለቤተሰብ፣ ለጎረቤት እና ለሀገር ቀና መስተጋብር መፍጠር ይገባል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በኢትዮጵያ የትኛውም የሀገር ጫፍ እና ክልል የሚያስፈልጋቸውን ነገር ማምረት እና ማዘጋጀት የማይችሉ በመሆኑ አንዱ ከአንዱ መስተጋብር ሊፈጥሩ እንደሚገባ አሳስበዋል።

አንዱ የሚሰጠውና የሚቀበለው በቁጥርና በዓይነት ሊለይ ይችላል እንጂ ሌላኛውን የማንፈልግ ብቻችንን በቂ የሆንን አይደለንም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፤ በጋራ የመኖርና የጋራ ተረክን መፍጠርና ማስፋፋት ለኢትዮጵያ አልፎም ለአፍሪካ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አስታውቀዋል።

የጋራ ግብ፣ ዓላማ፣ አጀንዳ፣ ራዕይ፣ መግባባት፣ መተባበር፣ ተነሳሽነት፣ ቆራጥነት፣ እጅን ንጹህ ማድረግ ቀና መስተጋብርን የሚፈጠሩ ዓብይት ጉዳዮች ሲሆኑ፤ እነዚህን ማሟላት የቻለ መስተጋብር ቤተሰብን፣ ሰፈርን፣ ሀገርን እና አህጉርን ወደ ብልጽግና መውሰድ እንደሚችል አመልክተዋል።

ግራ መጋባት፣ ግጭት፣ አለመደማመጥ እና ቀውስ ሀገርን የሚያፈርስ እና ቀና ያልሆነ መስተጋብርን የሚፈጥሩ በመሆናቸው ሁሉም ዜጋ ቀና መስተጋብርን ሊፈጥሩ እንደሚገባ አስታውቀዋል።

ዓለም የመስተጋብር ውጤት ናት፤ የትኛውም ሀብታም ሀገር ብቻውን መቶ በመቶ የሚያስፈልገውን ማዘጋጀት የሚችል የለም፤ በምንሰጠው ልክ ላንቀበል እንችላለን እንጂ ሳይቀበል ሳይሰጥ መቋቋም የሚችል ሀገር የለም ነው ያሉት፡

የተረክ መነሻው፣ መጀመሪያው እና አልፋው ማንነት መሆኑን ገልጸው፤ ሰው የተፈጠረበትን ማንነት ሲረዳ ወደ ታላቁ ትርክት መሄድና መድረስ የሚቻለው ብለዋል።

ትርክት በትክክል ከተኮተኮተ ትልቅ ሀገር ይፈጥራል፤ ካልተኮተኮተ ያዋጋል፣ ያጋድላል ያሉት ዐቢይ (ዶ/ር)፤ ዝም ብሎ መናገር ሳይሆን ክትትል ሊደረግለት እንደሚገባ ገልጸዋል።

ነጠላ ትርክት፣ ነጠላ ህልም፣ ነጠላ መዳረሻ፣ እና እንደዚህ የተዘበራረቀ ነገር ወደ አንድ ግብ የማይወስድ መሆኑን አስገንዝበው፤ በወል አስተሳሰብ፣ በወል ተሳትፎ እና በወል ውጤት ሰብሰብ ማድረግ ተገቢ መሆኑን ገልጸዋል።

# «ሠራዊቱ የሀገራችን የሉዓላዊነት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሠራዊቱ ሀገሩን ለመጠበቅ ሁሌም ዝግጁ ነው። በሌላ በኩል ሀገር እንዳይኖረን የሚፈልግ አካልና ከፍተኛ የውስጥ ቦርቧሪ አለ ብለዋል።

ኢትዮጵያን ለማዳከምና ለማፍረስ መከላከያን ማዳከምና ማፍረስ የሚል አጀንዳ አላቸው። እነዚህን በአግባቡ እንታገላቸዋለን። መሬት ላይ ያለውን ዕውነታ የማያውቁትንና ሠራዊቱን ለማፍረስ የሚመጡትን መታገል ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ለሀገራቸው ክብርና ለሠራዊቱ የሚሠሩትን እናበረታታለን ያሉት ፊልድ ማርሻሉ፤ ሀገር ለማጥፋት የሚጥሩትን እንደምንታገል ሁሉ ለሠራዊቱ በሙያቸው የሠሩትን ደግሞ የክብር አባል አድርገናቸዋል ብለዋል።

አሁን የክብር አባልነት ያገኛችሁ በሙያችሁ በእራሳቸው ተነሳሽነት ላደረጋችሁት ሁሉ ክብር ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

በመከላከያ ደረጃ 25 ለሆኑ ሰዎች በአንድ መድረክ የክብር አባልነት የተሠጠበት ጊዜ የለም። ሌሎችም ተመሣሣይ ሽልማቶች እንደሚኖሩ አስታውቀዋል።

ጥቅምት 15 ቀን የሚከበረውን 116ኛው የመከላከያ ሠራዊት ቀን አስመልክቶ በተዘጋጀው መርሐ-ግብር የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ በሙያቸው ባበረከቱት አስተዋጽኦ ለተመረጡ የክብር አባሎች የሜዳልያ ሽልማት አበርክተዋል።

የኢፕድ የፎቶ ባለሙያ ዳኜ አበራ፣ የኢቢሲ ጋዜጠኛ አበበች ካህሳይ፣ ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና፣ ጋዜጠኛ አርዓያ ተስፋማርያም፣ አበበ ቶላ (አቤ ቶኩቻው)፣ ናትናኤል መኮንን፣ ሰዩም ተሾመ የሠራዊቱን የክብር አባልነት ካገኙት መካከል ናቸው።

በመድረኩ የተለያዩ ሚኒስትሮች የመከላከያ ሠራዊት ከፍተኛ መኮንኖችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

በመድረኩ 25 የሚዲያ ባለሙያዎችና የማኅበራዊ ሚዲያ አንቂዎች እንዲሁም በማኅበራዊ ሚዲያ የተለያዩ ሥራዎችን ያከናወኑ አንድ የንግድ ሰው የመከላከያ የክብር አባል ሆነዋል።

በርካታ ሰዎችን በአንድ ጊዜ የመከላከያ ሠራዊት የክብር አባል የማድረጉ ሥራ በሠራዊቱ ታሪክ የመጀመሪያው ልምድ መሆኑን በመድረኩ ተገልጿል።

# ከሸቀጥና አልባሳት ሕገ ወጥ ንግድ ባሻገር- ኮንትሮባንድ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

እንደ ሀገር ጤናማና የተረጋጋ የሀገር ውስጥ ብሎም የጠረፍ ንግድ ሥርዓት መፍጠር እንዳልተቻለ ይገለጻል። ሕገወጥ ንግድ እየተባባሰ መጥቷል፤ ሕገወጥ ንግድ በሕገወጦች የሚከወን እንደመሆኑ ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ ሳይኖራቸው በንግድ ሥርዓቱ ውስጥ በተሰማሩ ሕገወጦች ሳቢያ ገበያ በከፍተኛ ሁኔታ እየተረበሸ ይገኛል። ይህም ለኑሮ ውድነቱ አንድ ምክንያት እየሆነ ቀጥሏል።

ሌላው የሕገወጥ ንግድ መልክ ኮንትሮባንድ ንግድ ነው። የኮንትሮባንድ ንግድ ከጤናማ የንግድ ሥርዓት የሚገኘውን ታክስ በከፍተኛ ደረጃ እየጎዳ ያለና አንዳንድ ሕገወጥ አካላት ኢ-ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ሀብት እንዲያፈሩ እያስቻለ ይገኛል። ይህ የኮንትሮባንድ ንግድ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ትልቅ አደጋ የጋረጠ ስለመሆኑ ከጉምሩክ ኮሚሽን የተገኘው መረጃ ያመላክታል። የኮንትሮባንድ ንግድ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያደርሰው አደጋ ሰፊ እንደሆነ ያመላከተው ኮሚሽኑ፤ በ2015 በጀት ዓመት ብቻ 80 ቢሊዮን ብር የተገመቱ የኮንትሮባንድ ቁሳቁስን በቁጥጥር ስር ማዋል እንደተቻለም አሳውቋል።

ኮሚሽኑ የችግሩን ግዝፈት የሚመጥን አደረጃጀት በመፍጠር እያከናወነ ባለው ተግባር በየዓመቱ በብዙ ቢሊዮን ብሮች የሚገመት የኮንትሮባንድ ቁሳቁስ በቁጥጥር ስር ሲያውል ቆይቷል። ያካሄደው ሪፎርም በኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ ላይ ጠንካራ ርምጃ እንዲወሰድ እያስቻለው መሆኑን ጠቅሶ፣ ይህን የሀገር ስጋት በመከላከልና መቆጣጠር በኩል ኃላፊነት የተሰጣቸው አንዳንድ ተቋማት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እየተወጡ ባለመሆናቸው ሳቢያ ችግሩን በሚፈለገው ልክ መቆጣጠር እንዳልተቻለ አስታውቋል።

ይህ በሀገሪቱ ላይ ትልቅ አደጋ የጋረጠና ልትሻገረው ያልቻለችው የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ እያስከተለ ካለው ኢኮኖሚያዊ ጫና ባለፈ በቀጣይ ሀገሪቱ በቀላሉ ልትወጣው ወደ ማትችለው ማህበራዊ ቀውስ ውስጥ ሊያስገባት እንደሚችል የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ያስገነዝባሉ። ችግሩን በቶሎ መከላከልና መቆጣጠር ካልተቻለና በዚሁ ከቀጠለ እንደ ሀገር ዘርፈ ብዙ ጥፋቶች ሊያስከትልና ሀገራዊ ዕድገትን በዘላቂነት ሊፈታተን ይችላል ሲሉም ነው ያመለከቱት።

**ኮንትሮባንድ የሀገር ኢኮኖሚን፣ የማህበረሰብን አጠቃላይ ዕድገት፣ ልማት፣ ደህንነት ያዛባል ብለን ካመንን ይህን ሲቃወም የሚችል ዜጋ መፍጠር ወሳኝና ዋና ሥራ ሲሆን ያስፈልጋል። ስትራቴጂክ በሆነ መንገድ ኃላፊነት ሲሰማው የሚችል ዜጋ መፍጠር ያስፈልጋል። ለእዚህም ከሥርዓተ ትምህርት /ካሪኩለም/ ጀምሮ መሥራት ተገቢ ነው**

የምጣኔ ሀብትና የሕግ ባለሙያው ዶክተር አያሌው አባተ ቢያሻው ፤ ሕገወጥ ንግድ ወይም ኮንትሮባንድ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ እንዲሁም በማህበራዊ እንቅስቃሴ ላይ እያሳደረ ካለው አሉታዊ ተጽዕኖ ባለፈ እንደ ሀገር ወደፊት የሚያስከትለው ጫና እጅግ ከባድ፣ ውስብስብና ፈታኝ መሆኑን መረዳትና ከወዲሁ መከላከል እንደሚገባ አጽንኦት ሰጥተው ይናገራሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ሕገወጥ ንግድ ወይም ኮንትሮባንድ በአገር ኢኮኖሚና የልማት እድገት ላይ እያሳደረ ያለው ተጽዕኖ እጅግ ከባድ ነው። በኢኮኖሚና ልማት እድገት ላይ እያሳደረ ካለው ተጽዕኖ ባሻገር በተለይም በሀገር ደህንነት፣ በሰላምና ጸጥታ፣ በገበያ አለመረጋጋት፣ ማህበራዊ መስተጋብሮችን በማዛነፍ፣ በመልካም አስተዳደርና በአካባቢ መራቆት ላይ እጅግ በጣም አደገኛ የሆነ ተጽዕኖ እያሳደረ ይገኛል።

ኮንትሮባንድ አሁን ላይ ብዙም ትኩረት ባልተደረገበት የአካባቢ መራቆት ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ ተጽዕኖ እያደረሰ ስለመሆኑ የጠቀሱት ዶክተር አያሌው፤ አካባቢን የሚያራቁቱ በርካታ ሕገወጥ ንግዶች እንደሚካሄዱ ጠቁመው፣ ከእነዚህም መካከል አንደኛው በፓርኮች ውስጥ በሚገኙ ሀብቶች ላይ የሚደረግ ሕገወጥ ንግድ መሆኑን ጠቅሰው፣ ለእዚህም የዝሆንን ጥርስና ኩንቢ ሕገወጥ ንግድን በአብነት ይጠቅሳሉ። ሁለተኛው ሕገወጥ የሆኑና የማይፈቀዱ የዕጾች ዝውውር ስለመሆኑ ጠቅሰው፤ እነዚህ ብዙም ትኩረት ያላገኙና በአካባቢ መራቆት ላይ እጅግ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ያላቸውና ዘላቂ የሀገር ልማትን ወደ ኋላ የሚጎትቱ ናቸው ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ሌላው ብዙም ትኩረት የማይደረግበት የኮንትሮባንድ ንግድ ሕገወጥ ማዳበሪያ ንግድ ነው። ይህም የሀገሪቱን ልማት ወደኋላ ይጎትታል። በሕገወጥ መንገድ የሚገባው ማዳበሪያ አንደኛ በሕገወጥ መንገድ በመግባቱ ሀገርን ገቢ ያሳጣል። ከዚህ በተጨማሪም ማዳበሪያው ጥራቱ የጠበቀ ባለመሆኑ አፈሩን የሚያመክንና እንዳያበቅል ያደርጋል። በመሆኑም ትክክለኛ ምርት መሰብሰብ አያስችልም፤ ነገ አፈሩን ማከም የማንችልበት ደረጃ ላይ በማድረስ ይጎዳዋል። ስለዚህ የአፈር ብክለት፣ የአየር ብክለትና የውሃ ብክለትን ሊያስከትሉ የሚችሉና ለሰው ልጆች ጤና ጠንቅ የሆኑ ሕገወጥ ንግዶች መሆናቸውን መረዳትና መከላከል ይገባል። በዚህ ላይ ሌሎች ሀገራት በከፍተኛ ሁኔታ ይሰሩበታል።

በማዕድን ዙሪያ የሚፈጸም ሕገወጥ ንግድም እንዲሁ ከፍተኛ ትኩረት የሚያሻውና በሕገወጥ ንግድ ሀገር ብዙ የምታጣበት እንደሆነ የጠቀሱት ዶክተር አያሌው፤ ሕገወጥ ንግድ ተብሎ ትኩረት የሚደረግባቸው በተለያዩ ሸቀጦችና አልባሳት ላይ የሚስተዋሉትን እንደሆነ ተናግረዋል። ይሁንና ብዙ ድምጽ ያላገኙትና ሀገሪቱን በከፍተኛ ሁኔታ እየጎዱ ያሉት የአካባቢ መራቆትና ሕገወጥ የመሣሪያ ንግድ መሆናቸውን ነው ያስረዱት። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚያስፈልግ ያመለክታሉ።

የአልባሳቱና የሸቀጦች ሕገወጥ ንግድ የዛሬውን ኢኮኖሚ የሚጎዱ ጊዜያዊ ችግሮች መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ብዙም ትኩረት ያልተሰጠው የአካባቢ መራቆት ሕገወጥ ንግድ መሆኑን ይናገራሉ፤ ይህ ሕገወጥ ንግድ የነገዋን ኢትዮጵያ የሚጎዳ እና የመጪውን ትውልድ የመልማት መብት ከዛሬው የሚያጠፋ ነው ይላሉ። ድርጊቱ ሀገር እንደ ሀገር እንዳትቀጥል የሚያደርግ እንደሆነ አስገንዝበው፣ በመቆጣጠሩ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል።

ሕገወጥ ንግድ በኢኮኖሚ ረገድ የኑሮ ውድነት በከፍተኛ ደረጃ እንዲባባስ እያደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ አጠቃላይ ሀገሪቷ ማግኘት ከሚገባት ገቢ አንጻር ሕገወጥ ንግዱ ኢኮኖሚውን እጅግ በጣም እየጎዳ መሆኑን አመልክተዋል።

ሕገወጥ ንግድ ወይም ኮንትሮባንድ በሕገወጥ መንገድ ገንዘብ የሚገኝበት መሆኑን ገልጸው፣ ይህንኑ በሕገወጥ መንገድ የተገኘን ገንዘብ ንጹህ ለማድረግ የሚኬድበት መንገድ በራሱ ሌላ ሕገወጥ አሠራርን የሚከተል እንደሆነ ዶክተር አያሌው ይጠቁማሉ። የውጭ ምንዛሪን በማዛባት ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያስከትል እንደሆነም ነው ያመላከቱት። ከዚህ በተጨማሪ የሀገሪቱን የመረጃ መረብ ደህንነት ጭምር ተጠቅመው ሊሠሩ የሚችሉ ኮንትሮባንዶች ጥቂት ስላለመሆናቸው የጠቀሱት ዶክተር አያሌው፤ ኮንትሮባንድ ንግድ ከሽብርተኝነትና ከሳይበር ጥቃት ጋር አብሮ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ እንደሆነም አመላክተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ኮንትሮባንድ ለመሥራት ሲባል የሚፈጸሙ በርካታ ወንጀሎች ይኖራሉ፤ ኮንትሮባንዲስቶች ከትንሽ እስከ ትልቅ ባለሥልጣኑን ማባለግና የመረጃ ደህንነቱን ሃክ ማድረግ እንዲሁም የማሸበር ተግባር በመሥራት ቀውስ በሚፈጠርበት ጊዜ የሚፈልጉትን የኮንትሮባድ ሥራ ይሠራሉ።

በመልካም አስተዳደርም እንዲሁ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳርፍ ጠቅሰው፣ ስለዚህ ኮንትሮባንድ ወይም ሕገወጥ ንግድ ሲባል ከሸቀጦችና አልባሳት ባለፈ እንደዚህ ሰፋ ብሎ መታየትና ትኩረት ሊደረግበት ይገባል ብለዋል።

«ኮንትሮባንድ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ ከባድና የከፋ በመሆኑ በደንብ ሊሠራበት ይገባል» ያሉት ዶክተር አያሌው፤ በዋነኝነት የሀገሪቱን ሕግና አሠራር በሚገባ መፈተሽ ያስፈልጋል ይላሉ። ሕጋዊ አሠራሩ አንዳንድ ጊዜ ሕጋዊ ሆኖ ለሚሠራው ሰው እንቅፋት የሚሆንበት ጊዜ እንዳለም አመልክተው፣ ይህም ወደ ሕገወጥ መንገድ ሊወስደው የሚችል ሰፊ ዕድል መኖሩንና ይህን መከላከል እንደሚገባ ያስገነዝባሉ። ስለዚህ አሠራሩን ቀላልና ግልጽ ማድረግ፣ ተደራሽነትን ማስፋትና ዘመኑ በሚጠይቀው ልክ ዘመናዊ አሠራሮችን ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል ሲሉ ያስገነዝባሉ።

«ኮንትሮባንድ የሀገር ኢኮኖሚን፣ የማህበረሰብን አጠቃላይ ዕድገት፣ ልማት፣ ደህንነት ያዛባል ብለን ካመንን ይህን ሊቃወም የሚችል ዜጋ መፍጠር ወሳኝና ዋና ሥራ ሊሆን ገባል» ያሉት ዶክተር አያሌው፤ ስትራቴጂክ በሆነ መንገድ ኃላፊነት ሊሰማው የሚችል ዜጋ መፍጠር ይገባል ይላሉ። ከሥርዓተ ትምህርት /ካሪኩለም/ ጀምሮ መሥራት ተገቢ መሆኑንም ያመለክታሉ። ለዚህም በቀዳሚነት ሊሠሩ የሚገባቸው ብልሹ የአሠራሮችን ማስተካከል እንደሚገባ ጠቁመው፣ ይህ ካልሆነ በትክክለኛው መስመር መጓዝ እንደማይቻልም ይገልጻሉ።

«የኮንትሮባንድ ንግድን መንግሥትና የመንግሥት አሠራር ብቻ ሊፈታው አይችልም » ያሉት ዶክተር አያሌው፤ የግል ዘርፉን እንቅስቃሴ በጣም ነጻ ማድረግና መንግሥት ሙሉ አቅሙን ቁጥጥርና ክትትል ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ መሥራት የሚችልበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር እንደሚገባም ይጠቁማሉ። ዶክተር አያሌው ሕግ በአግባቡ ሊከበር እንደሚገባ ጠቁመው፣ ጠረፍ አካባቢ የሚገኙ የአሠራር ሥርዓቶችን ማጠናከርና በክህሎት፣ በዕውቀትና በሥነምግባር ላይ የተመሠረተ መዋቅራዊ አሠራር እንዲደራጅ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ያመለክታሉ።

ከዓለም አቀፍ ተቋማትና ከጎረቤት ሀገራት ጋር የትብብር ሥርዓቱን ማዘመንና ማጠናከር አስፈላጊና መሠረታዊ እንደሆነ ጠቅሰው፤ በተለይም ከአካባቢ መራቆት ጋር ተያይዞ ዛሬ በሚገባቸው ልክ መለየት ያልቻልናቸውንና በደንብ ያልታዩን ሕገወጥ ንግዶች ከኢኮኖሚያዊ ችግር ባለፈ ነገ ከነገ ወዲያ ማህበራዊ ቀውስ ሊያስከትሉ የሚችሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን በሀገር ላይ እንደሚያስከትሉ ይጠቁማሉ። በእዚህ ትኩረት ተደርጎ ሊሠራበት እንደሚገባም አስገንዝበዋል። እንዲህ አይነቶቹ የኮንትሮባንድ ንግዶች የሚያስከትሉት ቀውስ አሁን ላይታይ እንደሚችልና ቀስ በቀስ ጉዳት እንደሚያደርስ አመልክተዋል። ኮንትሮባንድ ንግድ ምን ያህል ሀገርን ሊጎዳ እንደሚችል በተከታታይ በማሳየትና በማስተማር ማህበረሰቡ ንቃተ ህሊናው እንዲያድግ መሥራት ሌላኛው መፍትሔ መሆኑንም አስታውቀዋል።

በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ ተባባሪ ፕሮፌሰር ዶክተር መስፍን መንዛ የኮንትሮባንድ ንግድ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ እያሳደረ ባለው አሉታዊ ተጽዕኖ ምክንያት ማህበረሰቡ እየተጋፈጣቸው ያሉ በርካታ ችግሮች ስለመኖራቸው ጠቅሰው፣ ሀገርም እንደ ሀገር በብዙ እየተፈተነች መሆኑን አመልክተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ሕገወጥ ንግድ ለዋጋ ንረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው ነው። አሁን ገበያ ላይ ያለው ሰው ሰራሽ የሆነ ዋጋም በሕገወጥ ንግድ ምክንያት የመጣ ነው። ሕገወጥ ንግድ በሚስፋፋበት ጊዜ ህጋዊ የሆኑ ነጋዴዎች ከጫወታ ውጭ ይሆናሉ። ሕገወጥ ንግድ ወይም ኮንትሮባንድ ንግድ በግልጽ የማይታይና በኔትዎርክ የሚሰራ እንደመሆኑ የተለያዩ የመንግሥት አካላት ጭምር የሚነካኩበትና ረጅም ሰንሰለት ያለው ነው። በዚህም አብዛኛው ሸማች ማህበረሰብ በብዙ መልኩ ተጎጂ ይሆናል።

ሕገወጥ ንግድን ህጋዊ ለማድረግ በሚደረግ ሙከራም ተጨማሪ ሕገወጥ የሆኑ ተግባራት ይፈጸማሉ የሚሉት ዶክተር መስፍን፣ ሕጋዊ መንገድን የማይከተሉ ሕገወጥ ነጋዴዎች በቅናሽ የሚሸጡ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ተባባሪ እንዳላቸው ያመለክታሉ። ሸማቹ ለምርቱ ካለው ፍላጎት የተነሳ እንዲሁም በሚኖረው መጠነኛ ቅናሽ በሕገወጥ መንገድ የሚሸጡ የተለያዩ ሸቀጦችን በመግዛት የሕገወጦች ተባባሪ የሚሆንበት ሁኔታ እንዳለም ይጠቅሳሉ። በዚህ ምክንያት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በአሁኑ ወቅት ሕገወጥ ንግድ እየተስፋፋ እንደመጣና ለሀገር ፈተና የሆነበት ጊዜ ላይ መደረሱን ነው ያመላከቱት።

በሕገወጥ ንግድ ወይም በኮንትሮባንድ ምክንያት ሸማቹ ላይ እየደረሰ ያለው ችግር እንዳለ ሆኖ መንግሥትም እየተጎዳ እንደሆነ ያነሱት ዶክተር መስፍን፤ ሕገወጥ ነጋዴው ለተገለገለበት መክፈል የሚገባውን ታክስ ባለመክፈሉ መንግሥት ማግኘት የሚገባውን ገቢ እንደሚያጣ ገልጸዋል። በዚህም ምክንያት ማህበረሰቡ በቂ የሆነ መሠረተ ልማት ማግኘት አይችልም። በመሆኑም ህዝቡ በሁለት መንገድ ተጎጂ ይሆናል ይላሉ።

ዶክተር መስፍን እንዳሉትም፤ ሕገወጥ ንግድ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽዕኖ እያደረሰ ይገኛል። በዚህም መንግሥትን ጨምሮ፣ ሸማቹና አምራቹም ጭምር ተጎጂ ናቸው። ነገር ግን የተወሰኑና በሕገወጥ ንግድ ሥርዓት ውስጥ የሚገኙት ብቻ ተጠቃሚ ይሆናሉ።

ይህንን እንደ ሀገር ፈተና የሆነውን ኮንትሮባንድ መከላከል በዋናነት ከመንግሥት የሚጠበቅ ተግባር መሆኑን ጠቅሰው እንደ ማህበረሰብ እያዳንዱ ዜጋ ተግባሩን ሊጠየፍና ተበባሪ መሆን እንደሌለበትም እሳቸውም ያስገነዝባሉ።

የመንግሥት የቁጥጥር ሥርዓቱን መፈተሽና ጠንካራ ክትትል ማድረግ አለበት የሚሉት ዶክተር መስፍን፤ በተለይም በሕገወጥ ንግድ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ አንዳንድ የመንግሥት አካላት ጭምር በመኖራቸው መንግሥት በአሠራር ሥርዓት ላይ ከፍተኛ የሆነ ክትትልና ቁጥጥሩን ጠበቅ በማድረግ እንዲሁም ጥናት ማካሄድ ይጠበቅባታል ነው ያሉት። ከመንግሥት በተጨማሪም እያንዳንዱ ዜጋ የድርሻውን ለመወጣት የሕገወጦች ተባባሪ ከመሆን መቆጠብና ከግል ፍላጎት ባለፈ እንደ ሀገር ሰፋ አድርጎ ማሰብ እንዳለበትም ያስገነዝባሉ።

የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር በቅርቡ እንዳመለከተው ፤ በኮንትሮባንድና በሕገ ወጥ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚሳተፉ አካላት የማጭበርበሪያ ዘዴዎች በርካታ ሲሆኑ፤ በተለይም በድንበሮች ስፋት ምክንያት የሚካሄደው ኮንትሮባንድ ሰፊ ነው።

በችግሩ ስፋት ምክንያት ከሪፎርሙ ወዲህ አደጋውን ለመከላከል እየተሠሩ ያሉ በርካታ ሥራዎች ስለመኖራቸው ከኮሚሽኑ የተገኘው መረጃ የሚያመላክት ሲሆን፤ በቀጣይም ከችግሩ ለመውጣት በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ የተቀመጠውን የፀረ ኮንትሮባንድና ሕገወጥ ንግድ ግብረ ኃይል የሚመራበትን ስትራቴጂ በሚገባ ተግባራዊ የማድረግ ሥራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አመላክቷል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ‹‹ልመና ከልክል›› የደፈጣ ለማኞች

**ዋስልኝ አየለ**

ባለፈው ሐሙስ ነው። ማታ 11፡50 አካባቢ የመንግሥት ሠራተኞች ማመላለሻ አውቶብስ (ፐብሊክ ሰርቪስ) ለመያዝ ወደ መቆሚያ ቦታው እየሄድኩ ነው። አራት ኪሎ የሚገኘው አራዳ ክፍለ ከተማ በር ላይ ባለው የአውቶብስ መቆሚያ ቦታ ላይ አንድ ዕድሜው በአሥራዎቹ መጀመሪያ ሊሆን የሚችል ልጅ የእግረኛ መንገዱ ላይ ወድቋል። ፖሊሶችን ጨምሮ ዙሪያውን በሰዎች ተከቧል።

አጠገቡ ስደርስ በአፍና አፍንጫው ደም የሚመስል ነገር ይወጣል። እኔም እንደማንኛውም ሰው እያዘንኩ ‹‹ምን ሆኖ ይሆን?›› እያልኩ ምን እንደማግዝ ግራ ገብቶኝ ሳለ፤ አንዲት ሴትዮ ከመጣሁበት ተቃራኒ አቅጣጫ በኩል ሰዎችን እየገፋፋች የወደቀው ልጅ ጋ ደረሰች። ወዲያውኑ ለተሰበሰበው ሰው ወደየጉዳያቸው እንዲሄዱ መናገር ጀመረች። በቁጣ እና በመሰላቸት ድምጸት ልጁ እንደዚያ የሚያደርገው አውቆ መሆኑን ተናገረች። ቃሉን በትክክል ባልሰማትም የሆነ የሚጠጡት ነገር መኖሩን ተናገረች፤ በአፋቸው የሚወጣው ደም እንዲመስል ማለት ነው። እንዲህ የሚያደርጉት ገንዘብ እንዲሰበሰብላቸው ነው እያለች ምክንያቱን ተናገረች።

እሷ እንደዚያ ስትናገር እኔ ተናደድኩ። እንዴት አይነት ጭካኔ ነው ልጁ እንዲህ ወድቆ፣ በአፍና አፍንጫው ደም እየወጣ ምንም ያልመሰላት? ብየ ተገረምኩ። የተሰበሰቡት ሰዎች እንዳይሸወዱ አስጠንቅቃ መንገዷን ቀጠለች። እኔም ግራ እየተጋባሁ ትንሽ አለፍ ብየ ቆምኩ። የሚሆነውን ነገር እያየሁ ሳለ ሰዎች አንድ አንድ እያሉ ሄደው አለቁ። የነበሩት ፖሊሶችም ሄዱ። ልጁ ብቻውን ተኝቶ ቀረ። አጠገቡ ደግሞ ቆማ የምትለምን ሌላ ልጅ አለች።

አሁንም ግራ እየተጋባሁ አንድ የማውቀው የሰርቪስ ተጠቃሚ መጣ። ያየሁትን ነገር ሳስረዳው ‹‹አጠገቡ ያለችው ልጅ ‹አውቆ ነው› እያለች ነበር›› አለኝ። ነገርየው መለመኛ ይሆን እንዴ? እያልኩ መጠራጠር ጀመርኩ። በዙሪያዬ ያሉ ሰዎችም እንዲህ አይነት ማጭበርበሪያዎች መኖራቸውን እየነገሩኝ የማታለል የልመና አይነቶች ላይ ስናወራ ቆየን።

በዚህ ሁኔታ ላይ እያለን ከቆምነው ውስጥ አንደኛው ‹‹እዩት እዩት እዩት ሲነሳ›› አለን። ዞር ብየ ሳይ ቀስ ብሎ ተነስቶ ተቀመጠ፣ አሁንም ቀስ ብሎ ተነሳ። ዙሪያ ገባውን አይቶ ወደ አስፋልቱ ገባ። እንደማንኛውም ሰው እየተራመደ አስፋልቱን ከተሻገረ በኋላ በከፍተኛ ፍጥነት ወደ ቅድስት ማርያም ወጣ።

እንዲህ አይነት ማጭበርበር በዓይኔ ሳይ የመጀመሪያዬ ነው። እግራቸውን፣ እጃቸውንና የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸውን እንደ ተዋናይ ‹‹ሜክ አፕ›› በመቀባት በአካል ጉዳተኛ ስም የሚያጭበረብሩ እንዳሉ ሰምቼ አውቃለሁ፤ በመገናኛ ብዙኃንም ዜና ተሰርቶበት ያውቃል። እንዲህ በዓይኔ ማየቴ ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ስለሆነ ብዙ ሲያስገርመኝ ቆየ።

ወዲያውኑ ወደ አዕምሮዬ የመጣው በእነዚህ ሰዎች ምክንያት ልመና የማጭበርበር ብቻ ተደርጎ መታየቱ ነው። በትክክል ችግር ያጋጠማቸው ሰዎች አጋዥ ማጣታቸው ነው። አውቆ ነው ተብለው መታለፋቸው ነው። በእነዚህ አጭበርባሪዎች ምክንያት ሰብዓዊነት መጎዳቱ ነው። ሰዎችን ተጠራጣሪ እንዲሆኑ ማድረጉ ነው።

‹‹ልመና ከልክል›› የሚባል እናቶች ሲሉ የምሰማው አባባል አለ። ትልልቅ ሰዎች እገዛ ያስፈልጋቸዋል። አብሯቸው ወጣት ሰው ካለ የሚያግዛቸው ሌላ ሰው አይኖርም። ያ አብሯቸው ያለው ወጣት ሰው ሸክም ወይም ሌላ ነገር ካላገዛቸው ‹‹ልመና ከልክል›› ይሉታል። ምክንያቱም እሱ አለ በሚል ሌሎች ሰዎችን ‹‹አግዙኝ›› ብለው መለመን ሊቸገሩ ነው። በእነርሱ ዓውድ ልመና ማለት ‹‹በእንተ ስማ ለማርያም›› እያሉ ምፅዋት መጠየቅ ብቻ አይደለም። እገዛ መጠየቅን ልመና ይሉታል። ለምሳሌ ሸክም አሸክሙኝ ለማለት ‹‹ለምኜ ነው ያሸከሙኝ›› ይላሉ። ሰዎችን የሆነ ነገር እንዳያደርጉ ለማባበል ‹‹እባክህ ልለምንህ›› ይላሉ።

እናም እነዚህ አጭበርባሪዎች እገዛና ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ‹‹ልመና ከልክል›› ይሆናሉ። ሰዎች ለተቸገሩ ሰዎች ድጋፍ እንዳያደርጉ እየከለከሉ ነው። በእነዚህ አጭበርባሪዎች ምክንያት ተጠራጣሪ እንሆናለን።

እነዚህ አጭበርባሪ ለማኞች የደፈጣ ለማኝ ናቸው። የደፈጣ ውጊያ እንዳለ ሁሉ የደፈጣ ለማኝም ኖረ ማለት ነው። የደፈጣ ውጊያ ማለት የግድ ከወንዝ ወይም ከዛፍ ወይም ከድንጋይ በአጠቃላይ ከሆነ ነገር ሥር መደበቅ ማለት ብቻ አይደለም። የደፈጣ ውጊያ ማለት የማታለያና የማጭበርበሪያ መንገዶችንም መጠቀም ነው። ሴት (ንፁሃን) በመምሰል፣ ነፍሰ ጡር በመምሰል፣ አካል ጉዳተኛ በመምሰል በአጠቃላይ በብዙ ማታለያ መንገዶች ጠላት ላይ ጉዳት ያደርሳሉ።

ልክ እንደዚህ ሁሉ የደፈጣ ልመናም ተጀምሯል። በተለምዶ ‹‹ሿሿ›› የሚባለው ታክሲ ውስጥ የሚደረገው ማጭበርበር የዚህ አካል ነው። ሰውነትን የተለያየ አይነት ቀለም በመቀባት መለመን የደፈጣ ልመና መሆኑ ነው። እነዚህ ሰዎች ከማጭበርበራቸውም ባሻገር እገዛ በሚያስፈልጋቸው ሰዎች ላይ እምነት እንዲጠፋ እያደረጉ ነው። ምክንያቱም በትክክል ችግር አጋጥሟቸው መንገድ ላይ የሚወድቁ ሰዎችም አሉ።

የዚህኛው ገጠመኝ ተቃራኒ የሆነ ሌላ ገጠመኝ ልጨምር። እኔ ያጋጠመኝን የነገርኳት አንዲት የሥራ ባልደረባዬ ሌላ ገጠመኝ ነገረችኝ። ገጠመኙን ሳጠቃልለው የሚከተለው ነው።

አራት ኪሎ የሚገኘው ንብ ባንክ ሕንጻ ፊት ለፊት ካሉት ጁስ ቤቶች አጠገብ ነው። አንድ በወጣትነት ዕድሜ ላይ የሚገኝ ሰው ድንገት አዙሮት ተሽከርካሪዎች ከሚያልፉበት አፋልት ላይ ወደቀ። ከእጁ ላይ ሰነዶች ተበተኑ። ሰነዶችን ሰባስበው ሲያዩት የትምህርት ማስረጃዎች ናቸው። አራት ኪሎ አደባባዩ ጋ ከሚገኘው ክፍት የሥራ ማስታወቂያ ቦርድ ላይ ሥራ ሲፈልግ ቆይቶ እያለፈ ነበር። ልጁ የወደቀው ለረጅም ሰዓታት ምግብ ስላልበላ ከድካም ጋር ረሃብ ፀንቶበት ነው። ሲያነሱት ሰውነቱ ሁሉ ይንቀጠቀጣል። የአንደኛው ጁስ ቤት ባለቤቶች ወደ ውስጥ አስገብተው የሚበላ ነገር ሰጥተውት እየተሻለው ሄደ።

ይህ ክስተት ውስጥን ያላውሳል። ይህ በድካምና ረሃብ የወደቀ ልጅ በትክክልም እገዛ ያስፈልገዋል። እገዛ የተደረገለት ምናልባትም አጋዦች ችግሩ እውነተኛ መሆኑን ስላረጋገጡ ይሆናል፤ ምናልባትም አጭበርባሪዎች መኖራቸውን ስላላወቁ ይሆናል። የትምህርት ማስረጃዎቹን ስላዩ ሥራ ፈላጊ መሆኑ አሳዝኗቸው ይሆናል። ምንም ይሁን ምን ግን ያ ልጅ በዚያች ሰዓት እገዛ ያስፈልገዋል። ያ ልጅ ነገ ትልቅ ደረጃ ሊደርስ ይችላል፤ ምናልባትም በዚች ሀገር ላይ ትልቅ ሚና የሚኖረው ሊሆን ይችላል። የተቸገረውም አጋዥ ቤተሰብ የሌለው ስለሆነ ብቻ ላይሆን ይችላል። በአጭሩ በዚያች ቅጽበት ተቸግሯል። ከሩቅ አካባቢ የመጣ ከሆነ ምግብ ሳይበላ ቆይቶ ይሆናል፤ ለታክሲ የተሰጠችውን ገንዘብ ምናልባትም ‹‹ሥራ እናስገኝልሃለን›› ለሚሉ አጭበርባሪ ደላላዎች ከፍሎት ይሆናል። ያም ሆነ ይህ ያ ልጅ በዚያች ቅጽበት እገዛ አስፈልጎት ከከፍተኛ ጉዳት ወይም ከሞት ዳነ ማለት ነው። ይህ የሆነው ሰብዓዊነት በተሰማቸው ሰዎች ነው።

የእነዚህ የደፈጣ ለማኞች ትልቅ ጉዳት እንዲህ አይነቱን የሰብዓዊነት መተጋገዝ ጥላሸት የሚቀባ መሆኑ ነው። መተማመን እንዳይኖር ማድረጉ ነው። ተጠራጣሪ እንዲንሆን ማድረጉ ነው። መቼም ድጋፍ ለማድረግ የጤና ምርመራ ልናደርግለት አንችልም።

ምንም እንኳን አጭበርባሪዎች በዚህ ትዝብት ተፀፅተው ይተውታል ባይባልም በእነርሱ ምክንያት ግን ሰብዓዊነታችን እንዳይጎድፍ። የተደረሰባቸውንም መቀጣጫ ማድረግና ማጋለጥ ይለመድ። ዋናው ነገር ግን በአጭበርባሪዎች ምክንያት የተቸገሩትን እንዳናልፍ!

# ዓለም አቀፍ

## ከፈረቃ ውጭ የነበረ አንድ ፓይለት በረራ ላይ ያለ አውሮፕላን ሞተር ለማጥፋት በመሞከር ተከሰሰ




ከፈረቃው ውጭ የነበረ አንድ አብራሪ እሑድ ምሽት 83 ሰዎችን አሳፍሮ ሲበር የነበረ የመንገደኞች አውሮፕላን ለመከስከስ በመሞከር ተከሰሰ። ግለሰቡ 83 ሰዎችን ለመግደል በመሞከር ክስ ቀርቦበታል። ተጠርጣሪው በአላስካ አየር መንገድ አውሮፕላን ውስጥ ከፓይለቶቹ ጀርባ ተቀምጦ እንደነበር አየር መንገዱ ገልጿል።

የፖሊስ መዝገብ እንደሚያሳየው ተጠርጣሪው ስሙ ጆሴፍ ዴቪድ ኤመርሰን ሲሆን ዕድሜው ደግሞ 44 ነው። 80 መንገደኞች የተሳፈሩበት አውሮፕላን ከዋሺንግተን ግዛት ወደ ካሊፎርኒያ እያቀና ነበር። ነገር ግን በረራው ወደ ፖርትላንድ ኦሬገን እንዲሆን ተደርጎ ተጠርጣሪው ያለምንም ግርግር በቁጥጥር ሥር ውሏል።

አላስካ አየር መንገድ በለቀቀው መግለጫ እንዳለው ከሥራ ፈረቃ ውጭ የነበረው አብራሪ ከፓይለቶቹ ጀርባ ተቀምጦ የነበረ ሲሆን "ሞተሩን ለማጥፋት ሞክሮ አልተሳካለትም።" የአላስካ አየር መንገድ የበረራ ቁጥር 2059 ሠራተኞች ክስተቱን ወዲያውኑ ለአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ አሳውቀዋል።

ከአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ ጋር በነበረው ግንኙነት አንዱ አብራሪ "አንድ ግለሰብ ሞተሩን ለማጥፋት እየሞከረ ይገኛል፤ ነገር ግን አሁን ምንም ዓይነት አደጋ እያደረሰ አይደለም" ብሎ ሲናገር ይሰማል። "ሲመስለኝ በቁጥጥር ሥር ውሏል" የሚለው ፓይለቱ አክሎ "እንዳረፍን ወዲያውኑ ፖሊስ እንዲመጣልን እንፈልጋለን" ሲል ተሰምቷል።

በሆራይዘን ኤር የሚመራው በረራው በሥፍራው ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ 11፡25 ተነስቶ ምሽት 1፡30 ሳን ፍራንሲስኮ ማረፍ ነበረበት። ነገር ግን በረራው ወደ ኦሬገን እንዲያቀና የተገደደ ሲሆን ምሽት 1፡18 ሰዓት ተነስቶ ወደ ታቀደለት መዳረሻው አምርቷል።

ከመንገደኞች መካከል አንዷ አብሪ ጋቬሎ ለኤቢሲ ኒውስ እንደተናገረችው መንገደኞች ስለተፈጠረው ነገር የሚያውቁት አልነበረም። ነገር ግን በድንገተኛ ሕክምና ምክንያት አውሮፕላኑ ሊያርፍ መሆኑ ከመንገደኞች መስተንግዶ ክፍል መስማታቸውን ትናገራለች።

የፖርትላንድ ፖሊስ፣ ኤፍቢአይ እና የአላስካ አውሮፕላን ምርመራ ከፍተዋል። ኤፍቢአይ ባወጣው መግለጫ ጉዳዩን መመርመር መጀመሩን ገልጦ "ከዚህ ክስተት ጋር በተያያዘ ሌላ ምንም ዓይነት ስጋት እንደሌለ ለመንገደኞች ልናስረግጥ እንወዳለን" ብሏል።

ከግድያ ሙከራ በተጨማሪ ተጠርጣሪው ኤመርሰን 83 የሰው ልጅ አደጋ ላይ የሚጥል ተግባራት በመፈፀም እንዲሁም አውሮፕላን አደጋ ላይ ለመጣል በመሞከር ተከሷል። ባለሥልጣናት ተጠርጣሪው መች ችሎት ፊት እንደሚቀርብ ያሉት ነገር የለም።

ሰኞ ዕለት የፌዴራል አቪየሽን አስተዳደር ለአሜሪካ አየር መንገዶች በላከው መመሪያ "ክስተቱ አሁን ዓለም ላይ እየሆነ ካለው ጋር የሚያያዘው ነገር የለም" ማለቱን ቢቢሲ ዘግቧል።

## የአውሮፓ ህብረት ኒጀር ላይ አዲስ የማዕቀብ ማዕቀፍ አጸደቀ



የአውሮፓ ህብረት በሀምሌ ወር የኒጀርን ፕሬዚዳንት ከሥልጣን ባወረደው የወታደራዊ አስተዳደር አባላት ላይ ማዕቀብ ለመጣል ማዕቀፍ ማጽደቁን አስታውቋል።

ርምጃው ለኒጀር አለመረጋጋት፣ ዴሞክራሲ እና የሕግ የበላይነት እጦት እንዲሁም ለአካባቢው ሰላም እና ደህንነት ጠንቅ የሆኑትን ለመቅጣት ያለመ መሆኑን ህብረቱ በመግለጫው አመልክቷል። ህብረቱ ማዕቀቡ የንብረት እና የጉዞ እገዳን የሚያካትት ርምጃ ነው ብሏል፡፡

የአውሮፓ ህብረት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ኃላፊ ጆሴፍ ቦሬል አዲሱ ማዕቀፍ ህብረቱ የኒጀርን ሰላም፣ መረጋጋትና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ድርጊቶችን በሚፈጽሙ ግለሰቦችና አካላት ላይ ማዕቀብ መጣል ይችላል ብለዋል።

"የእገዳ ርምጃው የንብረት ማገድ እና ለግለሰቦች እና ለድርጅቶች ገንዘቦችን ማገድን እንዲሁም ለግለሰቦች የጉዞ እገዳን ያካትታል" ብለዋል።

የቀድሞ የፕሬዚዳንታዊ ጠባቂ አዛዥ ጄነራል አብዱራሃማኔ ቺያኒ ፕሬዚዳንት መሀመድ ባዙምን ባለፈው ሀምሌ ወር ከሥልጣን አስወግደዋል። ከጅምሩ ወታደራዊውን ጣልቃ ገብነት ያወገዘው የአውሮፓ ህብረት፤ አዲሱ ማዕቀፍ የምዕራብ አፍሪካ ሀገራት የኢኮኖሚ ማህበረሰብ (ኢኮዋስ) ሀገሪቱን በፍጥነት ወደ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ለመመለስ የሚያደርገውን ጥረት ይደግፋል ብሎ እምነት ይዟል። ማዕቀፉ "ግልጽ መልእክት ይልካል። ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ዋጋ ያስከፍላል የሚል ነው" ማለቱን አናዶሉ ዘግቧል።

ይሁን እንጂ አዲሶቹ ርምጃዎች የሰብዓዊ ርዳታ እንቅስቃሴዎች ላይ ተጽዕኖ እንደማይኖራቸው ህብረቱ ገልጿል ሲል አል ዐይን ዘግቧል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

## ሀገሬ፤ ስላንቺ ካወቅነው...

ከገጽ 5 የዞረ

አምስቱ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ መሆኑን ተገንዝበናል።

በፓርኩ ዝሆን፣ ጎሽ፣ ጉማሬ፣ ከርከሮ፣ ድኩላ፣ ድፋርሳ፣ አጋዘን፣ አሳማ፣ ዝንጀሮ፣ ጦጣ፣ አንበሳ፣ ነብር፣ የዱር ድመት እና ሌሎችም ይገኛሉ። ከፓርኩ እስካውቶች እንደተነገረን የዱር እንስሳቱን ለማየት ከጥቅጥቁ ደን፣ ለውሃም ለምግብም የሚወጡበትን ሰዓት ብቻ ሳይሆን ድምጽና ኮቴ ሳያሰሙ መጓዝ የዱር እንስሳቱን በቅርብ ርቀት ለማየት ይረዳል። የጨበራ ጩርጩራ ፓርክ ሰፊ በመሆኑ በእግር ብቻ ከሚገባባቸው ስፍራዎች ውጭ የፓርኩን ዙሪያ ገባ ለመመልከት መኪና መጠቀም አስፈላጊ ነው። በፓርኩ ወደሚገኘው የተፈጥሮ ሐይቅ ሄድንና በእስካውቶቹ ብርታት ቀይ ጉማሬ ተመለከትን።

ለምሳ እረፍት ያደረግነው በፓርኩ ውስጥ በሚገኝ አንድ ሬስቶራንት ነው። የሬስቶራንቱ ባለቤት ፊቤላ ትባላለች። ፊቤላ፣ በትውልድ ፈረንሳዊ ስትሆን ባለቤትዋ ደግሞ ኢትዮጵያዊ ነው። ከዛሬ አስር ዓመት በፊት ወደ ፓርኩ የመጣችው ለአንክሮና ለተዘክሮ ቢሆንም ቅሉ፣ የስፍራው ውበት ማርኮ ካስቀራቸው ሰዎች አንዷ ናት። ፊቤላ አሁን ላይ ቁጥራቸው ቀላል ለማይባሉ ባለሃብቶች ሞዴል ሆና ተሞክሮዋን እያጋራች ትገኛለች። አንዳንዶችም የሷን ፈለግ በመውሰድ ለፓርኩ ጌጥ የሆኑ ልማቶችን እያለሙ ይገኛሉ።

ከምሳ በኋላ ጸሐይ እያዘቀዘቀች ስትመጣ በፓርኩ የሚገኙ እስካውቶች ዝሆንን እናሳያችሁ በሚል እንደ ጦስ ዶሮ ይዞሩን ጀመር። ከብዙ ጎሾች መሀል አንድ ግዙፍ ዝሆን አየን። "ሌሎቹ ጥቅጥቅ ባለው ደን ይገኛሉ።" አለ አንደኛው እስካውት። ገሚሶቻችን ቫይናኩላር፣ ገሚሶቻችን የመኪና ኮርቶ መጋላ አንዳንዶችም ኮረብታማ ቦታዎች ላይ ሆነን ይሆናል ያልነውን ዘዴ በመጠቀም ብዙ ዝሆኖች ሲርመሰመሱ ለማየት አጮለቅን። ነገር ግን ከአንዲቷና በአካልም ግዙፍ ከሆነችው ዝሆን በቀር ሌሎቹ የውሃ ሽታ ሆነው ቀሩ። ምናልባት ዝሆኖቹ የተደበቁበትን ቦታ ለማወቅ በሚል ድሮን ወደ ማእከላዊ የፓርኩ ስፍራ ተላከች። እሷም ብትሆን ለዛሬ አልተሳካም ብላ ተመለሰች።

ዝሆኖች በብዛት ሊገኙ ይችላል የተባለበት ቦታ ሁሉ ዞርን። የታገሰ ከሚስቱ ይወልዳል እንዲል ተረቱ፣ የኋላ ኋላ ከብዙ ድካም በኋላ ለዓይን ያዝ ሲያደርግ፣ በቁጥር በርከት ያሉ ዝሆኖች በወንዝ ዳርቻ ሲጓዙ ተመለከትን። በትዕግስት በመጠበቃችን የሃሳባችን ሞልቷልና ባየነው ነገር ውስጣዊ ደስታ ተሰማን። የጨበራ ጩርጩራ ፓርክ የመስክ ጉብኝት መጠናቀቁን ተከትሎ ከኮንታ አመራሮች ጋር የማስታወሻ ፎቶ ተነሳን። ኮይሻ የኃይል ማመንጫ ወደሚገኘው ማረፊያችን ሄደንና አዳራችንን በዛው አደረግን።

በነጋታው ጠዋት፣ የኮንታ ዞን ጉብኝታችንን ማጠናቀቃችን ተነግሮን ሻንጣችንን ሸክፈን ወደ ኮስተሮቹ መኪናዎች ወጣን። ምስጋና ለኮይሻ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ሠራተኞች ይሁንና የተሰበረው ባሌስትራ እዚያ ተጠገነ። የጉዞ መዳረሻችን ዳውሮ ዞን መሆኑ ተነግሮን ወደዛው አመራን። ትንሽ እንደተጓዝን የአፈር ቁፋሮ ላይ የሚገኘው የመንገድ ሥራ፣ ሌሊቱን ዘንቦ በነበረው ዝናብ ላቁጦ ወደ አቀበት የሚወጡትን መኪኖች ወደኋላ ይጎትታቸዋል። ሁሉም መኪኖች ከፊታቸው በሚገኝ ስካባተር ጋር በካቦ ታስረው እየተጎተቱ ወጡ። የሙያ ባልደረቦቻችን የመንገዱን ችግር መፍትሔ ያገኘ ዘንድ ትእይንቱን በምስል አስቀሩት።

የዳውሮ ዞን ከተማ የደረስነው ስምንት ሰዓት ላይ ነበር። ከተማዋ ነቃ ያለች እና አልፎ አልፎም ፎቆች የሚታዩባት ናት። ከብዙ ኪሎ ሜትር ጉዞ በኋላ የአስፋልት መንገድም የሚገኘው ከተማው ውስጥ እንጂ ከዛ በፊት አይታሰብም። ወደ አንደኛው ሆቴል እንድንገባ ተነገረንና የምሳ ቆይታ በዚያ አደረግን። የዳውሮ ሰማይ ዝናብ አርግዟል። በፕሮግራማችን መሠረት በከተማው ወደሚገኘው የኤትኖግራፊ ሙዚየም አመራን። በሙዚየሙ የዳውሮን ብሔር ባህል፣ ታሪክ፣ ወግ፣ አኗኗር የሚያሳዩ ቁሳቁሶች፣ ባህላዊ ልብሶች፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች እና ቅርሶች አንዱም ሳይቀር በአግባቡ ተሰድረዋል። ከጉብኝቱ ስንወጣ የብሔረሰቡ የሙዚቃ ቡድን አባላት የብሔረሰቡን ባህላዊ ልብስ ለብሰው ማራኪ ውዝዋዜ ቀልባችንን ለጥቂት ደቂቃም ቢሆን ሰቅዘው ያዙት።



የሃላላ ኬላ ሪዞርት

**በቁንጠኛ አሰራር ተጊጠው በተራራ ላይ ጉች ጉች ያሉትና የጎጆ ቤት ቅርጽ ያላቸው የማረፊያ ክፍሉቹ፤ ይሄ ይቀራቸዋል የማይባልላቸው ናቸው**



የዳውሮ ብሔረሰብ ኤትኖግራፊ ሙዚየም

የኤሌክትሪክ መብራት መጥፋቱ፣ የዳውሮ ከተማን የተወረረች አስመስሏታል። አልፎ አልፎ ካልሆነ በቀር በዳውሮ የመብራት አገልግሎት በቀላሉ የሚታሰብ አይደለም። የዳውሮ ዞን መብራት እንደልቧ ባታገኘውም ወርቅን እና ሌሎች የከበሩ ማዕድናት ባለቤት ናት። እራት ያገኘሁትን የአካባቢው ተወላጅ አንድ ጥያቄ አቀረብኩለት።

"ሕዝቡን አስተባብራችሁ፣ ለከተማዋ የሚበቃ ጀነሬተር መግዛት እንዴት አቃታችሁ?" ብዬ ጠየቅኩት።

"ገዝተን ነበር አለ።"

"እና ምን ሆኖ ነው?" ስል ሌላ ጥያቄ አስከተልኩ።

"አንዱ ሹመኛ ከዚህ ሲነሣ ጭኖ ይዞት ሄደ።" አለኝ።

"ወደ የት!?" አሁንም ጠየቅኩት።

"እኔንጃ!" ሰውየው መለሰ።

"ቢያንስ የራሳችሁ ንብረት ሲወሰድ እንኳን ወደየት ነው የሚሄደው ብላችሁ አትጠይቁም!?" ሌላ ጥያቄ አከልኩት።

"ጊዜው የማይጠየቅበት ነበር።" ብሎ የማያዳግም መልስ ሰጠኝ።

አጠገቤ የሚንተከተከው ለሆቴሉ ብቻ የሚያበራው ጀነሬተር በመኖሩ እራት ለመብላትም ሆነ ወደ ማደሪያ አልጋችን ላይ ለመስፈር አግዞናል።

ጠዋት 12፡00 ሲሆን ከከተማዋ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኘውን የድንጋይ ከሰል ማበልጸጊያ ቦታ ጎበኘን። በዞኑ ፍቃድ ከተሰጣቸው ስምንት ባለሃብቶች ስድስቱ የድንጋይ ከሰል በማበልጸጊያ ሥራ ጀምረዋል። ፍቃድ እንዲሰጣቸው ያመለከቱት 41 አልሚዎች ቢሆኑም፣ የአካባቢው ሥነ ምህዳር እንዳይጎዳ በሚል እሳቤ ለስምንቱ ብቻ እንደተሰጠ ሰምተናል። በሌሎች ማዕድን ዘርፍ መሰማራት ለሚፈልጉ ግን አሁንም በራቸው ክፍት እንደሆነ ነው የተነገረን።

በዳውሮ ዞን የነበረንን ቆይታ አጠናቀን ወደ ሃላላ ኬላ የሚወስደውን መንገድ ይዘን ወደፊት ተወነጨፍን። ወደ ሃላላ ኬላ የሚወስደው መንገድ የአዲስ አበባ ከተማን የአስፋልት ደረጃ ቢበልጥ እንጂ አያንስም። የጉዞ መዳረሻችን ወደሆነው የሃላላ ሪዞርት መድረሳችንን የሚያመለክተውን በር ጋር ደርሰናል። ድንቅ የሆነ የዲዛይንና የአርክቴክት ጥበብ ይታይበታል፣ በሪዞርቱ። የእንግዳ መቀበያ፣ የመሰብሰቢያ አዳራሹም ወደ 200 የሚጠጋ ሰው ይይዛል። በሰፊው የተንጣለለው የምግብ አዳራሽ (በአንድ ጊዜ 100 ሰዎች ማስተናገድ የሚችል ነው። የመዋኛ ገንዳ፣ እንዲሁም ከመለስተኛ እስከ ቅንጡ ወይም ቪ አይ ፒ የመኝታ ክፍሎች ንጹህ አየር እንዲያስገቡ ሆነው በከፍታ ቦታ ላይ ተገንብተዋል።

በቁንጠኛ አሰራር ተጊጠው በተራራ ላይ ጉች ጉች ያሉትና የጎጆ ቤት ቅርጽ ያላቸው የማረፊያ ክፍሎቹ፣ ይሄ ይቀራቸዋል የማይባልላቸው ናቸው። ሪዞርቱ በቦታው እንዲገነባ የተመረጠበት ምክንያት ስፍራው የሃላላ ኬላ ታሪካዊ ቅርስ መገኛ ብቻ ሣይሆን፣ በተራራው ግርጌ የሚገኘውና በግልገል ግቤ ሶስት ምክንያት የተፈጠረው የሰራው ሰው ሰራሽ ሀይቅ ነው።

ሃላላ፣ የዳውሮ ንጉስ መጠሪያ ስም ነው። ንጉሱ የዳውሮን ሕዝብ ከጠላት ጦር ለመጠበቅ የድንጋይ ግንቦች አስገንብቶ ነበር። ይህ ቅርስ የሆነው አጥር፣ ከደረቅ ድንጋይ የተገነባ ሲሆን አጠቃላይ ግንባታው ከ200 ዓመታት በላይ የፈጀና በሦስት ትውልድ ቅብብሎሽ የተጠናቀቀ ነው። ሥራው የተጀመረው በ16ኛው ክፍለ ዘመን በካቲ(ንጉስ) ሃላላ ዘመን ነበር።

ስፍራውም በዳውሮዎች ካቲ ሃላላ ኬላ በመባል የሚጠራ ሲሆን፣ ትርጉሙም የንጉስ ሃላላ ግንቦች ማለት ነው። ንጉሱ ከንግስና ዘመናቸው አብላጫውን ወይም 25 ዓመታት ለዚህ ሥራ እንዳዋሉት ይነገርላቸዋል። ስያሜው ከንጉስ ሃላላ ጋር መያያዙ፣ ግንባታው ፍጻሜውን ያገኘው በእሳቸው ዘመን ስለሆነ ነው። ሃላላ ኬላ 1225 ኪ.ሜ ርዝማኔ ያሉት ሲሆን፣ ሰባት በሮች አሉት። ዳራሚሳ ሚፃ፣ ጋራዳ ሚፃ፣ ዳራ ሚፃ፣ አባርጋ ሚፃ፣ ካላ ሚፃ፣ ሜልዶካሬ ሚፃ፣ አናይዶሎ ሚፃ ተብለው ይጠራሉ።

ይህን ድንቅ የመስህብ ስፍራ ከጎበኘን በኋላ የግልገል ግቤ ሶስት ኃይል ማመንጫ ወደፈጠረው ሰው ሰራሽ ሐይቅ በሪዞርቱ መኪኖች አመራን። ሐይቁ ውስጥ ብዙ የዓሳ ምርት ይገኛል። ዓሳ ስላችሁ፣ በየገበያው የምናገኛቸው ሥራ የተቀቡ የሚመስሉትን ዓይነት አይደሉም እዛ የሚገኙት። ከውፍረታቸው የተነሣ መረብም ዓይንም የሚሞሉትን ዓሶች አልኩኝ እንጂ። ይህን ሐይቅ በጀልባ ማቋረጥ ከቻላችሁ 50 ኪ.ሜ ከመንገዳችሁ ላይ ትቀንሳላችሁ። ነገር ግን መኪኖቹ በተለመደው መንገድ ይምጡ ያሉንን ሺጋ ምክር አደመጥን። እንደተነገረን ሐይቁን በሞተር ጀልባ ተሻገርነው።

ኮስትሮቹ በተጠበቁት ሰዓት ሳይመጡ የውሃ ሽታ ሆነው ቀሩ። ቀኑ መሸ። በአቅራቢያው ወደሚገኝ አንድ መኖሪያ ቤት ጠጋ ብለን የመኪኖቹን መምጣት በጉጉት መጠባበቅ ያዝን። ከብዙ ጥበቃ በኋላ ጢምቢራው እንደዞረ ሰካራም እየተንከላወሱ መጡ ፤ መኪኖቹ። የመዘግየታቸው ምክንያት አንደኛው መኪና ከስሩ የገባውን ሕጻን ለማትረፍ በሚል አደጋ ደርሶበት እንደሆነ ሰማን። መኪናው ግጭት እንደደረሰበት ግን እርግጠኛ እንድንሆን ያደረገን በሹፌሩ በኩል የሚገኘው በርና ከኋላም በቀኝ በኩል ያለው መስታወት አደጋ እንደደረሰበት ባየን ጊዜ ነበር።

ስለተፈጠረው አደጋ እያወጋን ወላይታ ሶዶ ከተማ ደረስን። ሰፊው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሃብቶች በወፍ በረር ቃኝተን፣ ሐመልማላዊው ምድር አጣጥመን ሳንጨርሰው፣ ጉዞአችን ተጠናቀቀ። ውብ ሀገሬ፣ ስላንቺ ካወቅነው፣ ያለወቅነው እጅግ ብዙ ነው።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## ከልጅነት እስከ እርጅና ለሀገር የተከፈለ መስዋዕትነት

**ሰሚራ በርሀ**

ከልጅነት እድሜያቸው ጀምሮ ሀገራቸውን ወክለው ሲከራከሩ፤ በየተሳተፉበት መድረክም ሆነ ከመሪዎች ጋር በሚያደርጉት ንግግር ከአላማቸው ዝንፍ ሳይሉ ከሀገርና ከወገን ጎን ቆመው አልፈዋል። የሀገራቸውን ክብር ለማስጠበቅም ይጠቅማል ብለው የሚያስቡትን መንገድ ሁሉ ይጓዛሉ። እውቀታቸውን ተጠቅመው ይፈፅማሉ፣ ይታገላሉ።

ጣልያን ኢትዮጵያን ለመውረር ከሌሎች ሀገራት ጋር ያወጣችውን እቅድም ሆነ ሴራ ለማጋለጥ በጊዜው ቅንጣት ታክል ሳይፈሩ ለሀገርና ለወገናቸው ሽንጣቸውን ገትረው ተከራክረዋል፤ ሞግተዋል።

ይህንን ሁሉ ሥራ ሲሰሩም አብዛኛውን የሕይወታቸውን ክፍል ኑሯቸውን ያደረጉት በሰው ሀገር ከጠላቶቻቸው ጋር ፊት ለፊት ተፋጠው ነበር። በአንድ ወቅት የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴር፣ የዲፕሎማሲ ሰው የንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የሕግ አማካሪ፣ የባህል አምባሳደር ፣ በወዳጆቻቸው ዘንድ ቅን ሰው ናቸው ይባልላቸዋል። እኚህ ሰው ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ይባላሉ።

ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ በ1904 ዓ.ም መጋቢት አምስት ከአዲስ አበባ በ35 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው የኦሮሚያ ክልል ደንቢ ቀበሌ ከአባታቸው አለቃ ሀብተወልድ ሀብቴ እና ከእናታቸው ወይዘሮ ያደግድጉ ፍልፍሉ ተወለዱ። የአክሊሉ አባት አለቃ ሀብተወልድ ሀብቴ የቤተክህነት ሰው በመሆናቸው እናታቸውም ሆኑ አለቃ ሀብተወልድ ልጆቻችው በዚህ መንገድ እንዲያልፉ ፍላጎታቸው ነበር። አክሊሉም ከወንድሞቹ ጋር ወደ እንጦጦ ራጉኤል አቅንተው መማር ጀመሩ።


የጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ታላቅ ወንድማቸው መኮንን ሀብተወልድ በ1911 ዓ.ም 25ተኛ ዓመት የልደት በዓላቸውን ሲያከብሩ የጉምሩክ ዋና መሥሪያ ቤት ዋና ሹም ተብለው ተመረጡ። በጊዜው አባታቸው አለቃ ሀብተወልድ ሀብቴነህ ካረፉ ስምንት ወራቸው ነበር። መኮንን ሀብተወልድም ሥራቸውን ከተረከቡ ከሁለት ወር በኋላ የእህታቸውን ሁለት ልጆች መክብብና አካለወርቅ እና ትንሹን ወንድማቸውን አክሊሉን ዘመናዊ ትምህርት እንዲማሩ በሚል ወደ አዲስ አበባ ለመውሰድ ፈለጉ፤ እናም የገና በዓልን አስታከው ወደ እናታቸው ወይዘሮ ያደግድጎ ፍልፍሉ ጋር ፍቃድ ለመጠየቅ ሄዱ።

አባታቸው አለቃ ሀብተወልድ ሀብቴ የቤተክህነት ሰው ስለሆኑ ልጆቻቸውም ድቁናን እንዲማሩ ይፈልጉ ስለነበር እመት ያደግድጉ ፍልፍሉን ለማሳመን ከባድ ሆነባቸው። መኮንን ሀብተወልድም ከእመት ያደግድጉ ፍልፍሉ ፍቃድ ለማግኘት ሲሉ የርሳቸውን የንስሃ አባት መምሬ ገብሬ ዮሃንስን አማላጅ እንዲሆኑ ይዘዋቸው ሄዱ። በስንት ልመናና ውትወታም እመት ያደግድጉ ፍልፍሉ አክሊሉን ብቻ እንዲወስዱ ሁለቱ ወንድማማቾች መክበብ እና አካለወርቅ ግን ተስፋ ስላላቸው በዚያው እየተማሩ እንዲቆዩ አሉ።

መኮንን ሀብተወልድም ጥር 11 ቀን 1911 ዓ.ም አክሊሉን ለመውሰድ ወደእንጦጦ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ሄዱ። አክሊሉ ግን ከወንድሞቹ ተለይቶ ለመሄድ ፍቃደኛ አልነበረም። መክብብና አካለወልድም አክሊሉ ከኛ ተለይቶ አይሄድም አሉ። መኮንን ሀብተወልድም እናታቸው እመት ያደግድጉ ፍልፍሉ ለአሁኑ የፈቀዱላቸው አክሊሉን ብቻ እንደሆነ እነሱን ደግሞ ሌላ ቀን ተመልሰው እንደሚወስዷቸው ቢነግሯቸውም እነሱ ግን ለመነጣጠል ፍቃደኛ አልነበሩም። መኮንን ሀብተ ወልድም በነገሩ በጣም አዝነው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።

ከዛ በኋላ እመት ያደግድጉ ፍልፍሉ ህልም አዩ። ህልማቸውም መኮንን ሀብተወልድ በክብር ልብስ አሸብርቀው በወርቀዘቦ የተለጠፈ ካባ ደርበው ባርኔጣቸውን አድርገው ሶስቱን ወንድሞቻቸውን አስከተለው በቤተ-መንግሥት እየዞሩ መሬት እየለኩ ሲሰጧቸው ይመለከታሉ። እመት ያደግድጉ ህልማቸውን በቀጥታ ከእግዚአብሔር የተነገራቸው መልዕክት አድርገው በመውሰድ የልጆቻቸው እድል በመኮንን እጅ መሆኑን አመኑ።

መኮንን ሀብተወልድ ይህንን ሲሰሙ ደስታቸው ወደር አልነበረውም። ከዚያም መክብብ አካለወርቅና አክሊሉ ጥር 24 ቀን 1911 ዓ.ም ከእንጦጦ ራጉኤል ተነስተው በበቅሎ አዲስ አበባ ገቡ ። በቀጣዩ ዓመት 1912 ዓ.ም መስከረም 20 ቀን በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ገብተው ትምህርታቸውን ጀመሩ። ከወንድማቸው መኮንን ሀብተወልድ ጋር ሲኖሩ ከትምህርታቸው መልስ « ምክር መስጫ » የሚል ፕሮግራም ነበራቸው። ፕሮግራሙ በቤት ውስጥ ይደረግ የነበረ ሲሆን ይህም በአክሊሉ ልብ ውስጥ የሀገር ፍቅር ስሜት እንዲሰርፅ አድርገዋል።



**ከ**ጣልያን ጦርነት በኋላ ኢትዮጵያ ላይ ስተፈፀመው ግፍ ካሳ ሊከፈል ይገባል ሲሉ ጠየቁ። ነገር ግን ጣልያን በጦርነቱ ወቅት የተሰሩ መሠረተ ልማቶች እንደ ካሳ ይቆጠር ሲሉ ነገሩን ቢያቀሉትም አክሊሉ ግን ያ የራሳቸውን ሃሳብ ስማስፈፀም ያደረጉት እንደሆነ በመሞገት 5ሚሊዮን ዶላር የነበረውን ካሳ 25 ሚሊዮን ዶላር እንዲሆን አድርገዋል

አክሊሉ በወንድማቸው ቤት ለስምንት ዓመት ከኖሩ በኋላ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለመማር ወደ ግብፅ አቀኑ። በጊዜው የውጭ የትምህርት እድል አግኝተው ከሄዱ ጥቂት ተማሪዎች መካከል አክሊሉ ሀብተወልድ አንዱ ናቸው። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በግብፅ በሚገኘው የፈረንሳይ አሌክሳንድሪያ የሊሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ1917-1923 ዓ.ም ተማሩ። ከዛ በኋላም ወደ ፈረንሳይ ተጉዘው በታዋቂው የሶርቦን ዩኒቨርሲቲ ገብተው የከፍተኛ ትምህርታቸውን ቀጠሉ።

በዚህ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሲቆዩ በተለያየ የትምህርት ፋካልቲዎች ገብተው በህግ ትምህርት ኤል ኤል ቢ እና በንግድ ትምህርት ክፍል አጣምረው በማማር ዲፕሎማ አገኙ ከ1933 - 1935 ዓ.ም ያለውን ጊዜ ደግሞ በኢኮኖሚ አመራር በሕገ መንግሥትና አስተዳደር የሕግ ዶክትሬት ልዩ ዲፕሎማ አግኝተዋል።

አክሊሉ ሀብተወልድ ስለኢትዮጵያ መሟገትና ሀገራቸውን በዓለም ዘንድ በበጎ ስሟ እንዲነሳ ማድረግ የጀመሩት ከተማሪነት ጊዜያቸው ጀምሮ ነበር። በግብጽ በሚማሩበት ወቅት የአሌክሳንድሪያው የኮፕቲክ ፓትሪያርክ ኢትዮጵያን ሊጎበኙ በመጡበት ወቅት 60 ልጆችን ላስተምር ብለው ጠይቀው ወደ ሀገራቸው ይመለሳሉ። ከዚያም እነዚህ 60 ልጆች ከኢትዮጵያ ተመርጠው ወደ ግብፅ ከሄዱ በኋላ ግን ላኩልኝ ያልኩት ስድስት ልጆች ነው እንጂ 60 አይደለም ብለው ቅሬታ አቀረቡ። በዚህም ምክንያት ለትምህርት የሄዱት ተማሪዎች ለእንግልት ተዳረጉ።

ከተማሪዎቹ መካከልም ሶስት ተማሪዎች ተመርጠው ከካይሮ እነ አክሊሉ ወደሚገኙበት ወደ አሌክሳንድሪያ ሄዱ። በጊዜው ከአክሊሉ ጋር ለትምህርት የተላኩት 20 የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ነበሩ። አክሊሉ የተማሪዎቹን ችግር ካደመጡ በኋላ ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን የነበራቸውን ትርፍ ልብስ ከሰጧቸው በኋላ ጉዳዩን ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት አስረድተው ከሚመለከታቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቤተክርስቲያን ባለስልጣናት እና ለፓትሪያርኩ የተማሪዎቹን ችግር ካስረዱ በኋላ አስፈላጊው እገዛ እንዲደረግላቸው ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

ይህ በደህና ሁኔታ ለስድስት ወር ከቆየ በኋላ ደግመው ተማሪዎች ችግር ላይ መውደቃቸውን ሰሙ። አክሊሉ ይህንን እንዳረጋገጡ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በቴሌግራም ካሳወቋቸው በኋላ እሳቸውም ኢየሩሳሌም ለሚገኘው ቆንሲል ለአቶ ጳውሎስ ትእዛዝ አስተላልፈው ተማሪዎቹ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱ አደረጉ። በዚህ ጊዜ አክሊሉ ተማሪ ስለነበሩ ወደ ፖለቲካ ውስጥ አይግቡ የሚል አስተያየት ከሚማሩበት ትምህርት ቤት አስተዳደር ይደርሳቸው ነበር።

አክሊሉ በፈረንሳይ ሶርቦን ዩኒቨርሲቲ ተማሪ በነበሩበት ወቅትም ጣልያን ኢትዮጵያን ለመውረር ስታስብ በጊዜው ደግሞ ጀርመን እንዲሁ ፈረንሳይን ለመውረር ፍላጎት የምታሳይበት ወቅት በመሆኑ ፈረንሳይ ከሞሶሎኒ ጋር በይበልጥ መቀራረብ ጀመረች። በሂደትም ፈረንሳይና ጣልያን አንድ ስምምነት ላይ ደረሱ። እሱም ጣልያን በኢትዮጵያ ላይ የምታደርገውን ፈረንሳይ እንዳትቃወም የሚል ነበር ።

አክሊሉ በዚህ ወቅት እጅግ በርካታ ሥራዎችን ሰርተዋል። በጊዜው በፈረንሳይ ምርጫ ይካሄድ ስለነበር ለምርጫው የሚወዳደሩ ሶስት ፓርቲዎች በጊዜው ፈረንሳይን ይመራ የነበረው የላቫል መንግሥትን በመቃወም ፓርቲዎቹ ንግግር በሚያደርጉበት መድረክ ላይ አክሊሉ ብቻውን እየተገኙ ኢትዮጵያ በሊግ ኦፍ ኔሽን ቀርባ አቤቱታዋን በምታሰማበት ጊዜ አቤቱታዋ እንዳይታይ ማድረጋቸውን ጨምሮ ሌሎች የኢትዮጵያን አቋሞች ያስረዱ ነበር።

በፓሪስ በሚኖሩበት ወቅት አንደኛው ጣልያን የኢትዮጵያን ስም ለማጉደፍና የወረራ ሀሳቧ ተቀባይነት እንዲያገኝ ኢትዮጵያውያን ኋላቀር የሆኑ ሕዝቦች መኖሪያ እና የባሪያ ንግድ የሚካሄድባት ሀገር ናት በማለት በተለያዩ መገናኛ ብዙኃኖችና በጋዜጦቻቸው ላይ ያሰራጩ ነበር። አክሊሉ ይህንን የፕሮፓጋንዳ ሃሳብ ለማክሸፍ ከተለያዩ ጋዜጦች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ኢትዮጵያ ጥንታዊትና ነፃነቷን አስጠብቃ የቆየች ሀገር መሆኗን ማስረዳታቸውን ቀጠሉ፤ ከዚህም በሻገር «ኒውስ ኦፍ ኢትዮጵያ» የሚል ጋዜጣ መስርተው በየጊዜው የኢትዮጵያን አቋም የሚያስረዱ ጽሑፎችን እና ጣልያን ኢትዮጵያ ላይ ስለምታደርገው ያልተገባ ነገር የሚያስረዳ ጽሑፍ ያትማሉ፤ በየጊዜው እራሳቸውም ይፅፋሉ።

አክሊሉ ሀብተወልድ ከልጅነታቸው ጀምሮ የሚያደርጉትን ተጋድሎ በመመልከት በ19 ዓመታቸው የጄኔቫ የኢትዮጵያ ዴሊጌሽን ኮሚሽን ዋና ፀሐፊ ሆነው ተሾሙ። በጊዜውም የኢትዮጵያ ዴሊጌሽን መሪ ከነበሩት ፊታውራሪ ተክለሃዋርያት ጋር በመሆን በጄኔቫ ስለኢትዮጵያ ይሟገቱ ነበር።

በፈረንሳይ የኢትዮጵያ አምባሳደር የነበሩት የብላቴን ጌታ ወልደማርያም ነበሩ። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴም አክሊሉን በፓሪስ የፕሬስ አታሼ አድርገው ሾሟቸው። ብላቴን ጌታ ወልደማርያም በህመም ምክንያት እያደረጉ ለረጅም ጊዜ ከሥራ ይቀሩ ነበር። በዚህም ምክንያት ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተወልድ በ22 ዓመታቸው በፈረንሳይ አምባሳደር ሆነው ተሾሙ።

አክሊሉ ከፈረንሳይ ከተመለሱ በኋላ በተለያዩ ኃላፊነቶች ላይ አገልግለዋል። አክሊሉ ሀብተወልድ በኢትዮጵያ ሥራቸውን ሲጀምሩ በምክትል ጽሕፈት ሚኒስቴር የጃንሆይ አማካሪ ሆነው ከመሥራት በሻገር የሚኒስትሮችን ሥልጣንና ተግባር በነጋሪት ጋዜጣ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲወጣ አድርገዋል። ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ምክትል ሚኒስቴር በየደረጃው አገልግለው ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆነው ተሹመዋል።

ጸሐፊ ትእዛዝ በኢትዮጵያ የተለያዩ ትልልቅ ተቋማትን ለማቋቋም በርካታ ሥራዎችን ሰርተዋል። የኢትዮጵያን ብሔራዊ ባንክ ለማቋቋም በጊዜው ኢትዮጵያ የምትጠቀመው የምስራቅ አፍሪካን ሽልንግ በመሆኑ የመቆጣጠር ሥራውን የሚሰሩት እንግሊዞች ነበሩ። የኢትዮጵያ ባንክ ሥፍራውም በእንግሊዝ ሆኖ ኢትዮጵያም ወርቋን የምታስቀምጠው እዛ ነበር። አክሊሉ ይህ መሆኑ ምናልባትም ወደፊት ከእንግሊዝ ጋር ብንጋጭ ሀብታችንን ሊከለክሉን ይችላሉ የሚለውን ቀድመው በመገመት ዋና ቢሮው በኢትዮጵያ እንዲሆን የባንኩ የቦርድ አባላትም ኢትዮጵያውያኖች እንዲሆኑ እና በጃንሆይ እንዲሾሙ አድርገው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲቋቋም አደረጉ።

አክሊሉ ሀብተወልድ ለኢትዮጵያ አየር መንገድ መመስረትም ዋነኛው ሰው ናቸው። የዩናይትድ ኔሽን ምስረታን አጠናቀው ሲመለሱ አሜሪካን በማህበር ኤርላይንስ እናቋቁም ብለው ይጠይቋቸዋል። እነሱም አይሮፕላንም ሆነ አብራሪ የላችሁም በማለት ይቋሟቸዋል። አክሊሉም ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ከጃንሆይ ጋር በመመካከር አንድ አውሮፕላን በብድር በመግዛት እና የማኔጅመንቱን ኢትዮጵያ እየከፈለች ለተወሰነ ጊዜ እንዲያስተዳድሯቸው አደረጉ። ከዚያም ቲ.ደብሊው.ኤ የተሰኘ አውሮፕላን ገዝተው ሥራ እንዲጀምር አደረጉ።

የሊግ ኦፍ ኔሽን ወደ ዩናይትድ ኔሽን ተቀይሮ ሲቋቋም አብዛኛው የአፍሪካ ሀገራት ነጻ አልወጡም ነበር። በምስረታው ላይ ከአፍሪካ ተሳታፊ ከነበሩት ሀገራት ኢትዮጵያ፣ ግብፅና ላይቤሪያ ብቻ ነበሩ። አክሊሉ ሀብተወልድም በዩናይትድ ኔሽን ምስረታ ላይ ተገኝተው ቻርተሩ በሚዘጋጅበት ወቅት በኢትዮጵያ በኩል ብዙ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ከዚህም ውስጥ ራሳቸው ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ የአክሊሉ ማስታወሻ በሚል በ1967 በፃፉት መጽሐፍ ላይ እንደጠቀሱት አንድ መንግሥት ሌላ ኃይል ሊያጠቃኝ ነው ብለው አቤቱታ በሚያቀርቡበት ጊዜ ሴኩሪቲ ካውንስሉ ሊሰበሰብ ይገባል የሚል ሃሳብ አቀረቡ። ይህንን ሃሳብ አሜሪካኖች የተቃወሙት ቢሆንም አክሊሉ ግን ጣልያን ኢትዮጵያን ለመውረር ምልክት በምታሳይበት ወቅት በሊግ ኦፍ ኔሽን ቀርበው አቤቱታቸውን ሲያቀርቡ አለመሰማታቸውን እና ተቀባይነት ያገኙት ጣልያን ሰላሳ ኪሎ ሜትር ወደ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ ነው በማለት ነገሩን ወደኋላ ተመልሰው አስረዱ። አሜንድመንቱም ተቀባይነት አግኝቶ አሁን ድረስ እያገለገለ ይገኛል።

አክሊሉ ሀብተወልድ ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመለስ በበርቱ ተከራክረዋል በተለይም የኤርትራን ጉዳይ ሁሉም ሀገር ከጥቅሙ አንፃር ይመለከተው ነበርና ለአክሊሉ ቀላል አልነበረም። በተለይም እንግሊዝ አሜሪካ ፈረንሳይና ሶቪዬት ህብረት ጉዳዩን ይበልጥ አወሳስበውት ነበር። ነገር ግን አክሊሉ እጅ ባለመስጠት በተለያዩ መድረኮች ላይ እየተገኙ መሪዎቹን ጭምር ለየብቻ እያነጋገሩ እ.አ.አ በ1950 በተባበሩት መንግሥታት ዓመታዊ ጉባኤ ኤርትራ እንደ አንድ ሆና ኢትዮጵያን በፌዴራል እንድትቀላቀል ተወሰነ።

አክሊሉ ሀብተወልድ ከጣልያን ጦርነት በኋላ ኢትዮጵያ ላይ ለተፈፀመው ግፍ ካሳ ሊከፈል ይገባል ሲሉ ጠየቁ። ነገር ግን ጣልያን በጦርነቱ ወቅት የተሰሩ መሠረተ ልማቶች እንደ ካሳ ይቆጠር ሲሉ ነገሩን ቢያቀሉትም አክሊሉ ግን ያ የራሳቸውን ሃሳብ ለማስፈፀም ያደረጉት እንደሆነ በመሞገት 5ሚሊዮን ዶላር የነበረውን ካሳ 25 ሚሊዮን ዶላር እንዲሆን አድርገዋል። በጊዜው በእንግሊዝ ተይዛ የነበረችውን ጋምቤላን ለማስመለስ በአጼ ምኒልክና በእንግሊዞች መካከል የተፈረመውን እንግሊዝ በሱዳን እስከምትቆይ ድረስ ነው በማለት ሱዳን ነፃ ከመሆኗ ከሶስት ወር በፊት ሁለቱ መንግሥታቶች ተነጋግረው እንዲያስረክቡ ተስማሙ። አክሊሉም ጊዜው ሲደርስ የኢትዮጵያን ፖሊስ ወደ ቦታው ልከው የኢትዮጵያን ባንዲራ እንዲውለበለብ አደረጉ። ይህም ያለምንም ደም መፋሰስ የሰሩት ትልቅ ሥራ ነው። ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ነው ባገለገሉበት ወቅትም ለሀገር ሰላም ሲሉ ስልጣናቸውን በፈቃዳቸው የለቀቁ የመጀመሪያው መሪ ነበሩ።

ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ የንጉሠ ነገሥቱ አገዛዝ ወርዶ የደርግ መንግሥት ስልጣኑን ከያዘ በኋላ ኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም በጥቅሉ 60 በተለያየ ኃላፊነት ላይ የሚገኙ የሥራ ኃላፊዎች በተበየነባቸው የሞት ፍርድ ሕይወታቸው አልፏል። የቀብር ሥነ ሥርዓታቸውም የተፈፀመውም በዛው ቀን ነበር ።

# ስፖርት






## ሉሲዎቹ በኦሊምፒክ ወሳኝ የማጣሪያ ጨዋታ ጭልፊቶቹን ይገጥማሉ

**ብርሃን ፈይሳ**

የኢትዮጵያ ሴቶች እግር ኳስ ብሔራዊ ቡድን(ሉሲዎቹ) ለፓሪስ 2024 ኦሊምፒክ የማጣሪያ ጨዋታ ዛሬ ናይጄሪያን ይገጥማሉ። ሉሲዎቹ በደርሶ መልስ ጨዋታው ድምር ውጤት ማሸነፍ ከቻሉ ወደ ሶስተኛውና ወሳኙ የማጣሪያ ፍልሚያ የሚያልፉ ይሆናል። የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን በማህበራዊ ድረ ገጹ አማካኝነት ይህን ጨዋታ በቀጥታ እንደሚያስተላልፍም አስታውቋል።

ወራት የቀሩት የ2024ቱ የፓሪስ ኦሊምፒክ በእግር ኳስ ተሳታፊ የሚሆኑ ቡድኖች የሚለዩበት የማጣሪያ ጨዋታ በመከናወን ላይ ይገኛል። የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) በውድድር መድረኩ የሚወክሉትን ቡድኖች ለመለየት ጨዋታዎችን እያካሄደ ይገኛል። ዛሬ ከሚካሄዱ ጨዋታዎች መካከልም አዲስ አበባ አበበ ቢቂላ ስቴድየም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን (ሉሲዎቹ) እና ናይጄሪያ ብሔራዊ ቡድን (ጭልፊቶቹ) መካከል የሚካሄደው ጨዋታ ይጠበቃል። ሉሲዎቹ በመጀመሪያው ዙር የማጣሪያ ጨዋታ የቻድ አቻቸውን በሰፊ የግብ ልዩነት በመርታት ወደ ሁለተኛ ዙር ማለፋቸው የሚታወስ ነው። ዛሬ ከቀኑ 9ከ30 ላይም ሉሲዎቹ በሜዳና በደጋፊያቸው ፊት ወሳኝ ፍልሚያ ይጠብቃቸዋል።

በኦሊምፒኩ አፍሪካን ወክለው ተሳታፊ የሚሆኑ ሁለት ብሔራዊ ቡድኖችን ለመለየት የሚደረገው የማጣሪያ ጨዋታ አራት ዙሮች አሉት። በእነዚህ ዙሮችም በደርሶ መልስ በሚኖረው ጨዋታ አሸናፊ መሆን የቻሉ ቡድኖች ወደቀጣዮቹ ዙሮች ማለፍ ይችላሉ። ከወራት በፊት አዲስ አበባ ላይ ከቻድ ጋር በመጀመሪያው ጨዋታ 6 ለ ምንም በመርታት አስደናቂ ውጤት ያስመዘገቡት ሉሲዎቹ፤ ከቀናት በኋላም በሁለተኛው ጨዋታ 4 ግቦችን ከመረብ አሳርፈው በድምር ውጤት 10 ለምንም በማሸነፍ በቀላሉ ነበር ይህንን ዙር የተቀላቀሉት። በእጣ አወጣጡ መሠረትም የሁለቱ ቡድኖች አሸናፊ በአፍሪካ ሴቶች እግር ኳስ ትልቅ ስም ካላት ከጠንካራዋ ናይጄሪያ ጋር ለቀጣዩ ዙር ተፋላሚ ሆነዋል። ሉሲዎቹ ዛሬ የሚጠብቃቸውን ትልቅ ፈተና በደርሶ መልሱ ውጤት በድል መወጣት ከቻሉ በሶስተኛ ዙር ማጣሪያ ጨዋታ ከካሜሮን እና ኡጋንዳ አሸናፊ ጋር የሚገናኙ ይሆናል።



ሉሲዎቹ በኦሊምፒክ ማጣሪያ ናይጄሪያን ለማሸነፍ ተዘጋጅተዋል፣

ሉሲዎቹ ለዚህ ጨዋታ የሚሆነውን ዝግጅት ለአንድ ሳምንት ያደረጉ ሲሆን ዛሬ በሜዳቸው በሚያደርጉት ጨዋታ አሸናፊ ሆነው ማጠናቀቅ በቀጣይ የሚኖራቸውን እጣ ፈንታ የሚወስን ነው። ለዚህ የማጣሪያ ጨዋታ የቡድኑ ዋና አሰልጣኝ ፍሬው ኃይለገብርኤል ባለፈው ሳምንት ለ25 ተጫዋቾች ጥሪ ያደረጉ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ሃዋሳ ከተማ እና መቻል አብዛኛዎቹን ተጫዋቾች ያስመረጡ ክለቦች ናቸው። የቡድኑ አባላት ከተሰባሰቡበት ጊዜ አንስቶም ልምምዳቸውን በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ፣ ሃያ ሁለት በሚገኘው ሻላ ሜዳ እንዲሁም በመስቀል ፍላወር አካባቢ ባለው 35 ሜዳ ሲያከናውኑ ቆይተዋል። ሙሉ ቡድኑ በመልካም ጤንነት ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ ቀላል ጉዳት ገጥሟት የነበረችው አማካይ ኒቦኒይ የን ከቡድኑ ጋር ተቀላቅላ ትናንት እስከተካሄደው የመጨረሻው ልምምድ መሥራት ችላለች።

በዛሬው ጨዋታ ሉሲዎቹን ከሚገጥሙት የናይጄሪያ ብሔራዊ ቡድን ተጫዋቾች መካከል አብዛኞዎቹ በሀገር ውስጥ ሊግ የሚጫወቱ ሲሆኑ፤ ከሀገር ውጪ ባሉ ክለቦች የሚጫወቱት ጥሪ የተደረገላቸው ከቀናት በኋላ አቡጃ ላይ ለሚደረገው የመልስ ጨዋታ መሆኑን ዘጋርዲያን አስነብቧል። ጭልፊቶቹ ለመጨረሻ ጊዜ በመድረኩ የተጫወቱት እአአ በ2008ቱ የቤጂንግ ኦሊምፒክ ነበር። በመሆኑም ወደ ታላቁ የስፖርት መድረክ በድጋሚ ለመመለስ ጫና ፈጥረው እንደሚጫወቱ ይጠበቃል።

አውስትራሊያ በቅርቡ ባስተናገደችው የሴቶች ዓለም ዋንጫ ተሳታፊ የነበሩት ጭልፊቶቹ 16 ውስጥ መቀላቀል ችለው እንደነበረ አይዘነጋም። ይሁንና ከእንግሊዝ ብሔራዊ ቡድን ጋር በመለያ ምት በመሸነፋቸው ከዚያ በላይ ሊጓዙ አልቻሉም። በአፍሪካ ጠንካራ ከሚባሉ ቡድኖች መካከል የሚጠቀሱት ጭልፊቶቹ በዓለም ዋንጫ ተከታታይ ተሳትፎ ያላቸው ሲሆን፤ እአአ በ2000 እና 2004 በኦሊምፒክ መድረክ ተሳታፊ ነበሩ። በአቴንስ ኦሊምፒክ ተሳትፏቸውም እስከ ሩብ ፍጻሜ መጓዝ ችለው ነበር።


## ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በ2016 በጀት ዓመት የሚገለገልባቸውን እቃዎችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል:: **በዚህም መሠረት**

ሎት 1 ቴሌቪዥን እና ተዛማጅ መሳሪያዎች ግዥ

ሎት 2 የድምፅ ምስል ገመዶች የተለያዩ ኮኔክተሮች፤ የኔትዎርክ ገመዶች ግዥ

ሎት 3 የስቱዲዮ መብራት ግዥ

በጨረታ ቁጥር አ.ሚ.ኔ.ብ.ግ.ጨ..010/2016 በግልጽ ጨረታ ተጫራቾችን አወዳድሮ ለመግዛት የሚፈልግ

**በመሆኑ በጨረታው ለመሳተፍ የምትፈልጉ፡-**

1. በዘርፉ የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር የከፈሉና የገቢዎች ክሊራንስ ያላቸው
2. የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር የምዝገባ ሰርተፍኬት ማቅረብ የሚችሉና፣ በግዥ አቅራቢነት የተመዘገቡ::
3. ተጫራቾች በሚያቀርቡት እያንዳንዱ ሰነድ እና ፖስታ ላይ የድርጅቱን ማህተምና ፊርማቸውን ማኖር ይጠበቅባቸዋል::
4. ተጫራቾች ለሚያቀርቡት አጠቃላይ ዋጋ የጨረታ ማስከበሪያ ብር ለሎት 1. 300,000.00 ብር፣ ለሎት 2. 200,000.00 ብር፣ ለሎት 3 100,000.00 ብር በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
5. ተጫራቾች የጨረታውን ዝርዝር የሚያሳይ የጨረታ ሰነድ ይህ ማስታወቂ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ 10 /አስር/ የስራ ቀናት ውስጥ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ቢሮ ቁጥር 28 ለእያንዳንዱ ሰነድ የማይመለስ ብር 300.00 /ሦስት መቶ ብር/ በመክፈል ዘወትር በሥራ ሰዓት መግዛት ይችላሉ:: ጨረታው በ11ኛው ቀን ከቀኑ 4፡00 ተዘግቶ በዚሁ ቀን ከቀኑ 4፡30 ተጫራቾች/ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ቢሮ ቁጥር 10 ይከፈታል፡፡ ሆኖም ግን የተጫራቾች አለመገኘት ጨረታውን ከመክፈት አያግደውም፡፡ የመክፈቻው ዕለት በዓል/ዕረፍት ቀን ከሆነ በቀጣዩ የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ተዘግቶ ይከፈታል፡፡
6. ተጫራቾች የመወዳደሪያ ሃሳባቸውን ዋናውንና ኮፒውን / ቴክኒካል ኦሪጅናልና ኮፒ፣ ፋይናንሻል ኦሪጂናልና ኮፒ በተለያየ ፖስታ በማሸግ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ የጨረታ ሳጥን ማስገባት ይጠበቅባቸዋል፡፡
7. በአንዱ ተጫራች ዋጋ ላይ ተንተርሶ ዋጋ ማቅረብ የተከለከለ ነው፤
8. በጨረታ ያሸነፈ ተጫራች ከመ/ቤታችን ጋር ጨረታውን እንዳሸነፈ ካወቀበት ጊዜ አንስቶ በ15 ቀናት ውስጥ በሲፒኦ የጠቅላላ ዋጋውን 10% በማስያዝ ውል መዋዋል ይኖርበታል፡፡
9. ተቋሙ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻ**

የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ 5 ኪሎ ቅድስት ማሪያም ቤ/ክርስቲያን ከማህበረ ቅዱሳን ጀርባ ያለው ህንፃ ::

**ለበለጠ መረጃ ስልክ** 011 1 11 63 82/011 1 56 23 98 መደወል ይችላሉ፡፡

**የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**



## ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ

የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር በ2016 በጀት ዓመት በድሬዳዋ ከተማ B+G+3 ሕንፃ /B+G+3 Mixed Use Building/ ኮንትራክተሮችን በግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ አወዳድሮ ማስገንባት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህም ለግንባታው አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን በማሟላት የሚሰሩ ኮንትራክተሮች ደረጃቸው GC-5/BC-4 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ኮንትራክተሮችን በጨረታ አወዳድሮ ማሰራት ይፈልጋል፡፡

ስለዚህ በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ ድርጅቶች ሁሉ ይህ የጨረታ ማስታወቂያ በጋዜጣ ላይ ታታሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ሕዳር 14 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ድረስ ለዚሁ ሥራ የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ የማይመለስ ብር 400.00 /አራት መቶ ብር/በመክፈልና በመግዛት መወዳደር ይችላሉ፡፡

ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ማስያዝ ያለባቸው ብር 500.000.00/ አምስት መቶ ሺህ ብር/ በሲፒኦ /CPO/ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ጋራንቲ/Unconditional Bank Guarantee from Recognized Bank of Ethiopia/ ማስያዝ አለባቸው፡፡

ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ውስጥ የተገለጹትን የቴክኒካል ሰነዶችን የያዘ አንድ ዋናና እና ሁለት ኮፒ ለየብቻው እንዲሁም የፋይናንሻል ሰነድ የያዘ አንድ ዋናና ሁለት ኮፒ ለየብቻው እና የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትናውን ለየብቻው በፖስታ በማሸግ ሁሉንም በአንድ ትልቅ ፖስታ በማድረግ እስከ ሕዳር 14 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ድረስ ብቻ ለዚሁ ሥራ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ገቢ ማድረግ አለባቸው፡፡

ጨረታው ህዳር 14 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ታሽጎ በእለቱ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በሚገኙበት ህዳር 14 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ፒያሳ ጣይቱ ሆቴል አጠገብ በሚገኘው የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ዋና መ/ቤት ይከፈታል፡፡

አስተዳደሩ ስለጨረታው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር** 011-1267816 ደውሎ መረዳት ይቻላል፡፡

**የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር**